# መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት

## 3ኛ መጽሐፍ

## ዶክትሪን 3

## ክ ር ስ ቲ ያ ን   በ ዚ ህ   ዓ ለ ም

# ማውጫ


**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚያስተምረው ትምህርት** ገጽ

1. የቤተ ክርስቲያን መመሥረት . . . . . . . . . . . . . . 1
2. የቤተ ክርስቲያን አሠራር . . . . . . . . . . . . . . . 3
3. የቤተ ክርስቲያን ራስ፥ አካልና አባላት . . . . . . . . . . 5
4. የእግዚአብሔር ቤተሰብና የሚደረግለት እንክብካቤ . . . . . . . 6
5. የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ኑሮ . . . . . . . . . . . . 8
6. መንፈሳዊ ስጦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . 10
7. ጥምቀት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12
8. የጌታ እራት . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
9. የቤተ ክርስቲያን ተቋም . . . . . . . . . . . . . . . 16

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚያስተምረው ትምህርት**

10. ጋብቻ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው . . . . . . . . . . . 21
11. በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ የባልና ሚስት የሥራ ድርሻ . . . . . . 22
12. የክርስቲያን ጋብቻ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . 24

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት የሚያስተምረው ትምህርት**

13. ጸሎት ምንድን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . 26
14. ጸሎት የሚደረግባቸው ምክንያቶችና ውጤታቸው . . . . . . . . 27
15. የጸሎት ዕንቅፋቶች . . . . . . . . . . . . . . . . 30
16. ክርስቶስ በጸሎት ያሳየው ምሳሌነት . . . . . . . . . . . 31
17. የጌታ ጸሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . 33
18. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ታላላቅ ጸሎቶች . . . . . 35

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጨረሻ ነገሮች የሚያስተምረው ትምህርት**

19. ሞት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 38
20. ትንሣኤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40
21. የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት . . . . . . . . . . . . . . 43
22. የወደፊቱ ሁኔታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . 46
23. የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት . . . . . . . . . . . . . . 50
24. ፍርድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 52
25. የዘመን መጨረሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . 55

# መ ጽ ሐ ፍ  ቅ ዱ ስ  ስ ለ  ቤ ት  ክ ር ስ ቲ ያ ን
# የ ሚ ያ ስ ተ ም ረ ው  ት ም ህ ር ት
## ጥናት አንድ
## የቤተ ክርስቲያን መመሥረት (ማቴ.16፡1-20)

### የጥናቱ ዓላማ

የቤተ ክርስቲያንን መመሥረትና «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ እንድንረዳ ነው።

### መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን የማይነጣጠሉ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ጥንስሳ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቢሆንም እንኳ በተለይም የአዲስ ኪዳን ተቋም ናት። የቤተ ክርስቲያንን አመሠራረት ሥርዓት ተልዕኮና የጥንት ታሪክ የምናገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። ስለዚህ አዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን መመሪያ መጽሐፍ መሆን አለበት። በቤተ ክርስቲያን የሚታዩት አብዛኛዎቹ ጉድለቶች የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችን በማዛባት ወይም አጣምሞ በመተርጎም ሳቢያ የመጡ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

1. ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው ማን ነው?

   ሀ. ኢየሱስ «እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ?» ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። ጴጥሮስም «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም በዚህ በጴጥሮስ የእምነት ምስክርነት መሠረት የአዲስ ኪዳንን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ፤ ማቴ.16፡15፥16፥ 18።

   ለ. እውነት የሆነውን ምስክርነት ለጴጥሮስ የገለጠለት እግዚአብሔር ነበር፤ ማቴ.16፡17።

   ሐ. በበዓለ አምሳ ዕለት ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የመሰከረው ጴጥሮስ ነበር። በእርሱም ምስክርነት ሦስት ሺህ ሰዎች በክርስቶስ አመኑ። ይህም የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተመረጡት ሰዎች የመጀመሪያው ሸንጎ ሆነ።

   መ. የቤተ ክርስቲያን እምነት መመሪያ የሆነው የሐዋርያት ትምህርተ ክርስትና ነበር።

2. «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

   ሀ. በግሪክ ቋንቋ «ኤክሌሲያ» የሚለው ቃል የተመረጡ ወይም «የተጠሩ» ሰዎች ጉባኤ ወይም ሸንጎ ማለት ነው።

   ለ. ከሌሎች አሕዛብ እንዲለዩ ከብሉይ ኪዳን የአይሁድ ስብሰባ ወይም ሸንጎ ሁሉ የተጠሩ ሰዎች ጉባኤ ነበር። በዚህ አሳብ መሠረት በሐዋ. ሥራ 7፡38 ቤተ ክርስቲያን ተብለው ተጠርተዋል።

ሐ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕንፃውን ሳይሆን ሕዝቡን ነው።

መ. ስለዚህ «ቤተ ክርስቲያን» ማለት የናዝሬቱ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን የተነገረለት መሲህ ነው የሚለውን መለኮታዊ መገለጥ የሚቀበሉና በሐዋርያት በተላለፈው ትምህርት ላይ ኑሮአቸውን የሚመሠርቱ ሰዎች ማኅበር ማለት ነው።

3. ቤተ ክርስቲያን እነማን ናቸው?

ሀ. እንደ ጴጥሮስ ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምነው የሚመሰክሩ ሰዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

ለ. ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሲጠቀስ ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው በክርስቶስ ያመኑትን የአጥቢያ ጉባኤ ነበር። ይህም በአጠገባችን የሚገኝ በቅርብ ማየት የምንችለው ቤተ ክርስቲያን ነው።

ሐ. አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል አጠቃላይ ትርጉም ይኖረዋል፤ ይህም አንድ የተወሰነ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን በተለይ በዚያን ወቅት ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ያመለክታል። ለምሳሌ የሐዋ.8፡3 ተመልከቱ።

መ. ጳውሎስ በኤፌሶን፣ በቆላስያስና በዕብራውያን መልዕክቶች ውስጥ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል የሚጠቀመው በማንኛውም ዘመን የሚገኙ የእውነተኛ አባሎች አካል ለማለት ነው።

## ጥያቄዎች

1. «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?
2. ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በየትኛው ምስክርነት ላይ ነው?
3. የቤተ ክርስቲያን የእምነት መመሪያ ምንድን ነው?
4. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን «በበረሃ ያለች ቤተ ክርስቲያን» ተብለው የተጠሩት ለምን ነበር?
5. በኤፌሶን 2፡19-22 የተጻፈው ሐሳብ ትርጉም ምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያኑ መሠረት የሆነውን የእምነት መመሪያ በግልጽ አውጇል። እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባልና ቤተ ክርስቲያን በተለይ ሊታወቁበት የሚገባ ኑሮ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት አዲስ ኪዳን በግልጽ ያብራራል። እንግዲህ በዓለም አብረን ከምንኖራቸውና ከምንሠራቸው ሰዎች መካከል በተለይ «የተጠሩ» የሚያሰኘን ሕይወት አለን?

በክርስቲያን ኅብረት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር «ምርጦች» ላይሆኑ ይችላሉ። በስንዴም ውስጥ ጥቂት እንክርዳድ አለ። ታዲያ የእኛ ድርሻ ምን መሆን ይገባዋል?

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ነበር፤ ኤፌ.2፡20፤ 1ኛ ተሰ.1፡1፤ 1ኛ ጢሞ.3፡15።

የሐዋርያት ትምህርተ ክርስትና የእምነት መመሪያ ነበር፤ የሐዋ.2፡42፤ 4፡33።

«ቤተ ክርስቲያን» በብሉይ ኪዳን፤ የሐዋ.7፡38፤ ዘሌ.4፡13።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፤ የሐዋ.5፡11፤ 8፡1፤ 11፡2፤ 11፡26፤ 14፡23፤ 18፡22፤ 20፡17። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ብዙ ክርስቲያኖችን ይጠቁማል፤ የሐዋ. 8፡3፤ 1ኛ ቆሮ.15፡9፤ ገላ 1፡13፤ ፊልጵ.3፡6፤ የሐዋ.9፡31፤ ሮሜ 16፡23፤ 1ኛ ቆሮ.10፡32።

የእግዚአብሔር «ምርጦች» ማለት በማንኛውም ዘመን የሚገኙ እውነተኛ አማኞች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተብለው ተጠርተዋል፤ ቆላ 1፡18፥ 24፤ ዕብ.12፡23፤ ኤፌ.1፡22፥ 23፤ 3፡10፤ ማቴ.16፡18።

# ጥናት ሁለት

# የቤተ ክርስቲያን አሠራር (የሐዋ.ሥራ 13)

## የጥናቱ ዓላማ

ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ሥልጣንና ተግባር ተረድተን በዘመናችን ባሉት አብያተ ክርስቲያናት እንድንገለገልባቸው ነው።

## መግቢያ

ጌታችን ቤተ ክርስቲያንን ያቋቋመው በዓለም ላይ የምታከናውነው ተግባር ስላላት ነው። ጌታ ሥራውን የመቀጠሉን ኃላፊነት ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷታል። በአማኞች አካል ሥራውን ይሠራል። በክርስቲያኖች አንደበት ይናገራል፤ በእጆቻቸው ይገለገላል፤ በእግሮቻቸው በሰዎች መካከል ይመላለሳል።

1. ቤተ ክርስቲያን ለክርስቲያኖች የምትሰጠው አገልግሎት፡-

   ሀ. ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ኅብረት ታስገኛለች፤ የሐዋ.13፡2-3። በሐዋርያት ዘመን ክርስቲያኖች በየቤቱ ይሰበሰቡ ነበር።

   ለ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል መማሪያ ጉባኤ ነው፤ የሐዋ.13፡15-42። በሐዋርያት ዘመን ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ቃል በአይሁድ ምኩራብ አስተማሩ፤ የሐዋ.13፡5፥ 14።

   ሐ. ቤተ ክርስቲያን የተገለፀውን እውነት ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ጠባቂ ናት፤ 1 ጢሞ.3፡15፤ 2ኛጢሞ.2፡15፤ ይሁዳ 2፡3።

   መ. ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ላልሰሙ እንዲያዳርሱ ሰዎችን ትልካለች፤ የሐዋ.13፡3-5።

2. ቤተ ክርስቲያን ላላመኑት የምትሰጠው አገልግሎት፡-

   ሀ. ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የምታዳርስ የእግዚአብሔር ወኪል ናት። ቤተ ክርስቲያን ለማንም ሳታዳላ ላልዳነ ሰው ሁሉ ወንጌልን መመስከር አለባት፤ የሐዋ. 13፡2-4፥ 14፥ 42፥ 48። ይህም በክርስቶስ የተሰጠ ተልዕኮ ነበር፤ የሐዋ.1፡8።

   ለ. ቤተ ክርስቲያን ለድሆች አገልግሎት መስጠት አለባት፤ ገላ.2፡10።

3. የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት፤ የሐዋ.13፡2-3።

ሀ. በማቴ.16፡16-18 እንደምንመለከተው ሐዋርያት ሥልጣናቸውን የተቀበሉት ከክርስቶስ ከራሱ ነው። ክርስቶስም ኃይልን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸዋል፤ ማቴ.28፡18-20።

ለ. በሐዋ.13፡2-3 የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች ሊጾሙና ሊጸልዩ ባርናባስ እና ሳውልን ለአገልግሎት እንዲልኩ መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው እናነባለን።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን ሥልጣኗን ከእግዚአብሔር ትቀበላለች፤ መንፈስ ቅዱስም የሚያስፈልገውን ኃይል ይሰጣታል።

## ጥያቄዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ኃይልን ከየት እንደምትቀበል የሚያስረዱ ሦስት ጥቅሶችን ጻፉ።
2. ቤተ ክርስቲያን ለአባሎችዋ ያለባት ኃላፊነት ምንድን ነው?
3. ወንጌልን ለአሕዛብ እንዲሰብኩ በአንጾኪያ ያለችው ቤ.ክ. በርናባስንና ሳውልን በማን ሥልጣን ላከቻቸው?
4. ቤተ ክርስቲያን ላልዳኑት ያለባትን ተግባር የምታከናውነው በምን መንገድ ነው?

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ በጥንት አብያተ ክርስቲያናት እንዳደረገ ሁሉ አሁንም ቤተ ክርስቲያንንና እያንዳንዱን አባል ሊመራ ይችላል፤ ይመራልም።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ጋር ሊነጻጸሩ የሚችሉት እንዴት ነው?

1. ቤተ ክርስቲያናችን ላልሰሙት ሰዎች ወንጌልን ታዳርሳለች? ወንጌላውያንንስ ትልካለች?
2. ቤተ ክርስቲያናችን አባላቷንና ልጆችዋን ሁሉ ቃሉን ታስተምራለች?
3. ቤተ ክርስቲያናችን ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ሥልጣን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ትለማመዳለች?
4. ቤተ ክርስቲያናችን ያለምንም ማዛባት ትምህርቷን ትጠብቃለች?

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ሐዋርያት በቤትና በቤተ መቅደስ አመለኩ፤ ጸለዩም፤ የሐዋ.2፡46-47፤ 3፡1፤ 12፡12። ሐዋርያት ወንጌልን በምኩራብ አስተማሩ፤ የሐዋ.14፡1፤ 17፡1-2።

ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ወኪል ናት፤ ዮሐ.17፡18፤ 20፡21።

ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ኃይል ያገኘችው ከእግዚአብሔር ነው፤ ማቴ.16፡16-18፤ 28፡18-20፤ የሐዋ.1፡8፤ ኤፌ.1፡22-23።

የቤተ ክርስቲያን ዓላማ፤ ኤፌ.1፡3-14፤ 3፡10፤ 5፡23-27፤ 1ኛጴጥ.2፡5።

መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ይመራል፤ ዮሐ.16፡13፤ የሐዋ.10፡19፤ 16፡6፤ ሮሜ 8፡14።

ቤተ ክርስቲያን ድሆችን መርዳት አለባት፤ ማቴ.25፡40፤ ገላ.2፡10፤ 1ኛ ዮሐ.3፡17፤ ያዕ.2፡15-17።

## ጥናት ሦስት

# የቤተ ክርስቲያን ራስ፤ አካልና አባላት (1ኛ ቆሮ.12፡1-30)

### የጥናቱ ዓላማ

እያንዳንዱ ብልት ለአካላችን ጠቃሚ እንደሆነ ሁሉ እኛ እያንዳንዳችን ለሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላትና የቤተ ክርስቲያን ራስ ለሆነው ለክርስቶስ ጠቃሚ ነን።

## መግቢያ

በ1ኛ ቆሮ.12 ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ቦታ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ፥ ድርሻቸውን የሚያከናውኑ፥ በክርስቶስ መሪነትም በአንድነት የሚሠሩ ብዙ አባላት ያሉባት መሆኗን ጳውሎስ ይነግረናል። እነዚህ አባላት እያንዳንዳቸው ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንመልከት።

1. ቤተ ክርስቲያን ሕያው አካል ነው፤ ራሱም ክርስቶስ ነው።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ በብዙ የተለያየ መንገድ፥ ቦታና ጊዜ እግዚአብሔርን ያመልካል። ይህም ቤተሰብ በአንድ ላይ የተያያዘ አንድ አካል አለው፤ ይኸውም ከራሱ ከክርስቶስ ጋር በመንፈስ ቅዱስ የተጣመረ ነው፤ 1ኛ ቆሮ.12፡12-14፤ ቆላ.1፡18።

2. ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት፡-

   ሀ. ቤተ ክርስቲያን ወይም ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የተመረጡት ሰዎች በእምነት በክርስቶስ ያሉና የመንፈስ ፍሬዎችንም የሚገልጹ ናቸው፤ 1ኛ ቆሮ.12፡13፤ ዮሐ.15፡8፤ ኤፌ.4፡15፤ ቆላ.2፡19።

   ለ. ራሳችንና አካላችን ሊነጣጠሉ እንደማይችሉ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ አንድ አካልና ሕይወት ናት፤ 1ኛ ቆሮ.12፡12-14።

   ሐ. ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምንጭ ነው፤ በራስነቱም የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና ጠባቂ ነው፤ ኤፌ.5፡23-24፤ 1፡23።

   መ. ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይተባበራል፤ ራሱንም ይገልፅባታል፤ ኤፌ.4፡15፤ ቆላ.2፡19።

3. የቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት፡-

   ሀ. የአንድ አካል ብልቶች በመሆናቸው እያንዳንዱ የሚያከናውነው የራሱ ድርሻ አለው፤ 1ኛ ቆሮ.12፡4፥ 5፥ 6።

   ለ. አንዱ ብልት ሲታወክ ሌሎቹም አብረው ይሰቃያሉ፤ 1ኛ ቆሮ.12፡26።

   ሐ. እያንዳንዱ ብልት የአካሉ ክፍል በመሆኑ ለሌሎች ብልቶች ጠቃሚ ነው፤ 1ኛ ቆሮ.12፡14-17፥ 21-22።

   መ. የምናፍርባቸው ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል፤ 1ኛ ቆሮ.12፡24።

ሠ. አንዱ ብልት ሌላውን ሊያንፀው ይገባል፤ 1ኛ ቆሮ.12፡4-7።

ረ. የመንፈስ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት አንዱ ሌላውን እንዲያገለግልና እንዲያንፅ ነው፤ 1ኛ ቆሮ.12፡4-12።

## ጥያቄዎች

1. የክርስቶስ አካል አንድ የሆነው በምን መንገድ ነው?
2. ለቤተ ክርስቲያን አባላት አንዱ የሌላው ዕርዳታ የሚያስፈልገው እንዴት ነው?
3. ለደካማ ብልቶች እንክብካቤ መደረግ ያለበት እንዴት ነው?
4. ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለው ዓላማ ምንድን ነው?
5. አንዱ ብልት ሌላውን እንዴት ሊያገለግል ይችላል?

## ማጠቃለያ

የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበባችሁ በኋላ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፍቅር የቱን ያህል ታላቅ እንደሆነ ተወያዩበት። ዘካ.2፡8፤ 9፡16፤ ሚልክ.3፡17፤ የሐዋ.20፡28፤ ኤፌ.5፡25።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

1. ራስ፡- ኤፌ.1፡22-23፤ 4፡3-6፤ 5፡23፤ ቆላ.1፡8-24፤ 2፡19።
2. ሙሽራ፡- ማቴ.9፡15፤ 25፡1፥ 6፤ ዮሐ.3፡29፤ ራዕ.21፡2፤ ሮሜ 7፡4፤ 2ኛ ቆሮ.11፡2።
3. አባት፡- 2ኛ ቆሮ.6፡18፤ ሮሜ 8፡5፥ 17።
4. ወንድሞችና እህቶች ከክርስቶስ ጋር አብረው ወራሾች ስለመሆናቸው፡- ማቴ.12፡50፤ ሮሜ 8፡17፤ ዕብ.2፡11፤ ሮሜ 8፡29፤ ራዕ.12፡10።

# ጥናት አራት

# የእግዚአብሔር ቤተሰብና የሚደረግለት እንክብካቤ

# (ኤፌ.2፡11-22)

### የጥናቱ ዓላማ

የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሚያደርገንና በእርሱም ውስጥ መሆናችንን የሚያረጋግጥልን ክርስቶስ እራሱ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው።

## መግቢያ

የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሚያደርገን እግዚአብሔር እራሱ ነው።

«ፀጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፤» ኤፌ.2፡8።

1. የእግዚአብሔር ቤተሰብ በመሆን የሚገኙ በረከቶች፡-

ሀ. ከክርስቶስ ውጭ ያሉት ሰዎች ሁኔታ፤ ኤፌ.2፡12፡-

1. ከክርስቶስ ተለይተዋል።
2 . የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አያውቁም።
3 . ተስፋና እግዚአብሔር የላቸውም።

ለ. ክርስቶስ ለሚያምኑት የሚሰጣቸው ጥቅም፤ ኤፌ.22፡13-17፡-

1. ወደ እግዚአብሔር ኅብረት ያመጣቸዋል።
2. የልብ ሰላም ይሰጣል።
3. በዘሮች መካከል ያለውን ልዩነትና ጥላቻ ያስወግዳል።
4. አዲስ ፍጡር ያደርጋቸዋል።
5. ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቃል።
6. የሚያምኑትን ሁሉ የአንድ ቤተሰብ አባል ያደርጋቸዋል።

ሐ. በክርስቶስ ውስጥ ያሉት የሚያገኙት በረከት፤ ኤፌ.2፡18-22፡-

1. በክርስቶስ ያሉ ከቅዱሳን ጋር ተካፋዮችና የእግዚአብሔር ቤተሰብ ይሆናሉ። ሁሉም አንድ ቤተሰብ ይሆናሉ።
2. መንፈስ ቅዱስ የሚያድርባቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይሆናሉ።
3. እነርሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሲሆኑ ክርስቶስ የማዕዘን ራስ ይሆናል።
4. የክርስቶስ አካል ብልቶች ይሆናሉ። የዚህ አካልም ራስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን አምነን ስንቀበል እርሱ አዳኛችን ይሆናል፤ ከዚያም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች እንሆናለን። በምድር ላይ ቤተሰቡ በአንድነት ሲሰበሰብ እንግዶች ይኖራሉ። ከራሳችን በስተቀር እንግዶቹ ወይም አባሎቹ እነማን እንደሆኑ እናውቅ ይሆናል።

2. የእግዚአብሔር ቤተሰብ የአባላቱን ንጽሕና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤ 1ኛ ቆሮ. 5።

ሀ. ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ኃጢአት አስገንዝቧል፤ 1ኛ ቆሮ.5፡1። ለችግሩም ራሳቸው መፍትሔ እንዲፈልጉለት ትቶላቸዋል።

ለ. ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በመካከላቸው የነበረውን ኃጢአት ችላ ስላሉ ገስጿቸዋል፤ 1ኛ ቆሮ.5፡3-5።

ሐ. ጳውሎስ ኃጢአቱ ስለሚያስከትለውም ጉዳት አስጠንቅቋቸዋል፤ 1ኛ ቆሮ.5፡6-13። ትንሽ ኃጢአት በሊጥ ውስጥ እንዳለ እርሾ ነው። በቤተ ክርስቲያን ያለ ኃጢአት ወዲያውኑ ካልተወገደ የመላውን ቤተ ክርስቲያን ምስክርነት፣ መንፈስና ኃይል ይበክላል።

መ. ክርስቲያኖች በፍቅር በመመካከር አንዱ ሌላውን የመገሰጽና የማስጠንቀቅ ኃላፊነት አለባቸው፤ ሉቃ. 17፡3፤ የሐዋ.20፡31፤ 2ኛ ጢሞ.4፡2።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሚያደርገን ማን ነው?
2. ክርስቶስን ያላገኘ ሰው ምን ዓይነት ሁኔታ ይታይበታል?
3. በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች የሚያገኙአቸውን ሦስት በረከቶች ወይም ጥቅሞች ዘርዝሩ።

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሥራ መሠረት የአንድ ቤተሰብ አባላት ስለሚያደርገን መንፈስ ቅዱስ በልቡ የሚሠራበት ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነው።

የአንድ አካባቢ ክርስቲያኖች ለአገልግሎትና ለአምልኮ ሲሰበሰቡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ እነርሱ ብቻ አለመሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው። በስብሰባው የሚገኙት ሁሉም የቤተሰቡ አባላት አይደሉም። በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ሥፍራ የቤተሰቡ አባላት ሲሰበሰቡ የክርስቶስ አካል አንድ ንዑስ ክፍል ብቻ መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ስንል የቤተሰቡን አባላት ብቻ ማለታችን ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ስብሰባ ለመካፈል የመጡትን ሰዎች ሁሉ ያጠቃልላል።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ቤተ ክርስቲያን እነማን ናቸው? ሮሜ 8፡14፤ 12፡5፤ ኤፌ.4፡15፤ 5፡30፤ ፊልጵ.2፡15፤ 1ኛ ዮሐ.2፡24።

ቤተሰቡ ክርኩሰት እንዲጠበቅ፡-

ማስጠንቀቅ፤ የሐዋ.20፡31፤ ቆላ.1፡28፤ 1ኛ ተሰ.5፡14።

መምከርና መገሰጽ፡- ቲቶ 2፡15፤ ሉቃ.17፡3፤ ቲቶ 1፡፡3።

የኃጢአት ውጤት መንገር፡- መዝ.65፡18፤ ኢሳ.59፡2፤ ገላ.6፡7-8፤ 1ኛ ቆሮ.5፡6-13።

# ጥናት አምስት

# የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ኑሮ (2ኛ ቆሮ.2)

### የጥናቱ ዓላማ

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረተ ሐሳቦች አማካይነት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ክርኩሰት ሁሉ እንድንጠበቅ ነው።

## መግቢያ

«እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ስለሚፈልግ» እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የቤተ ክርስቲያን ራስ ለሆነው ክርስቶስ መገዛት አለበት፤ ኤፌ.5፡27።

ጳውሎስ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» ብሏል፤ የሐዋ. 20፡28። ጳውሎስ በመጨረሻው ጉዞው ወቅት ለኤፌሶን ቤ.ክ. ሽማግሌዎች «እያንዳንዱን ቀንና ሌሊት በእንባ ከመገሰጽ አላቋረጥኩም» በማለት የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና ለመጠበቅ ምሳሌ ሆኗቸዋል።

1. ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረው ኃጢአት ምን አደረገ?

ሀ. በቤተ ክርስቲያኑ የነበረውን ኃጢአት ተረድቶ ጉብኝት በማድረግ ወይም በደብዳቤ አማካይነት ስለነገሩ አሳሰባቸው፤ 1ኛ ቆሮ.5፡1፤ 2ኛ ቆሮ.2፡4።

ለ. ጳውሎስ በነገሩ ውስጥ እጁን ሳያስገባ ኃላፊነቱን ለአጥቢያው ጉባኤ ተወ፤ 2ኛ ቆሮ.2፡9።

ሐ. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ በደሉን ችላ ብላ ተወችው፤ በኋላ ግን በደለኛውን ከልክ በላይ ቀጣችው፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡4-6።

መ. አሁን በደለኛው ንስሐ ስለገባ ይቅር ማለት፤ ማጽናናትና ፍቅራቸውንም ማደስ እንዳለባቸው ጳውሎስ ያሳስባቸዋል።

2. ስለ በደለኛው አባል የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ያለባት ኃላፊነት ምንድንነው?

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ኅብረት አባሎቹን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። ያልተናዘዙት ኃጢአት የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ያበላሻል፤ 2ኛ ቆሮ.11፡2።

ለ. ቤ.ክ. የምታደርገው ቁጥጥር በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ሐሳቦች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤ 2ኛ ተሰ.3፡14-15። እንደ አካባቢው ባህልና ሁኔታም መሆን አለበት።

3. የቅጣት ዓላማ ምንድን ነው? 2ኛ ቆሮ.2፡7-11፥ 14፥ 15።

ሀ. ሰይጣንን ኃይል ማሳጣት፥

ለ. የበደለኛውን በደል በማጥላላት በደለኛውን መርዳት፥

ሐ. የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ነውር የሌለበት እንዲሆን ማድረግና

መ. የክርስቶስን ስም ማስከበር ነው።

4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ንስሐ ያልገቡ በደለኞች ቅጣት ምንድን ነው?

ሀ. በአዲስ ኪዳን የተገለጸው ቅጣት በደለኛውን ከኅብረት ውጭ አድርጉት የሚል ብቻ ነው፤ ማቴ.18፡17፤ 1ኛ ቆሮ.5፡13። ሆኖም ይህ ቅጣት ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ላልሆኑ ክርስቲያኖች ብቻ የተወሰነ ነው።

ለ. አማኝ ንስሐ ከገባና መግባቱንም በሕይወቱ ካረጋገጠ ይቅርታ ሊደረግለትና እንደገናም ወደ ኅብረት ሊመለስ ይገባል።

5. ቤተ ክርስቲያን ንጽሕናዋን እንዴት ልትጠብቅ ትችላለች? 2ኛ ቆሮ.2፡14። የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን ክርስቶስን መታዘዝ ድል አድራጊ ያደርጋል፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡9፥ 14፤ 1ኛ ዮሐ.5፡4።

## ጥያቄዎች

1. የአጥቢያን ቤተ ክርስቲያን ችግር መፍታት ያለበት ማን ነው?

2. በቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የተስተካከለ ፍርድ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? ኃጢአትን ለማስወገድ መሞከር እንጂ ጭካኔ የማያስፈልግበት ምክንያትስ ምንድን ነው?

3. አንድ ሰው ከቤተ ክርስቲያን መወገድ ያለበት መቼ ነው? ለምን? ለምን ያህል ጊዜ?

4. ቤተ ክርስቲያን የአባሎችዋን ምስክርነት የምትቆጣጠርበት ዓላማ ምንድን ነው?

5. ቤተ ክርስቲያን ንጽሕናዋን ልትጠብቅ የምትችለው እንዴት ነው?

## ማጠቃለያ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሷንና የሌሎች አባላት ምስክርነትን ለመጠበቅ የአባሎችዋን ትምህርተ ክርስትናና አኗኗር የማረም የመቆጣጠር ሙሉ መብት አላት። የምእመናን ሙሉ ትብብር ካስፈለገ መላው ጉባኤ ሁኔታው ላይ መወያየትና መስማማት አለበት።

ጉባኤው ውሳኔው ለቤተ ክርስቲያኒቷ አገልግሎትና ምስክርነት ጠቃሚ መሆኑንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይቃረን መሆኑን ማመን አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ውሳኔ የማስተላለፍ ሥልጣን የለውም።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

<u>የቤተ ክርስቲያን ዓላማ</u>-ኤፌ.3፡10።

ቤተ ክርስቲያን ከግለሰብ ጋር ያላት ግንኙነት - ሮሜ 12፡4-5።

የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት፡-

- ለእርማት እንጂ ለበቀል አይደለም፤ 2ኛ ቆሮ.13፡2፥ 10።
- ሲያስፈልግ ይገስጻል፤ 1ኛ ጢሞ.5፡20፤ ማቴ.18፡15-17።
- ኃጢአትን መናዘዝ አስፈላጊ ነው፤ ያዕ.5፡16።
- የማይናዘዝ ሰው ከቤተ ክርስቲያን ይወገድ፤ 1ኛ ቆሮ.5፡1፥ 5፥ 13፤ 1ኛ ጢሞ.1፡20፤ ቲቶ 3፡10።

# ጥናት ስድስት

## መንፈሳዊ ስጦታዎች (ኤፌ.4፡1-16)

### የጥናቱ ዓላማ

እያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ ስጦታ የተሰጠው መሆኑንና በስጦታውም የእግዚአብሔርን ቤት ማለት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ያለበት መሆኑን ለመረዳት እንዲችል ነው።

## መግቢያ

እግዚአብሔር ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም አስተምሩ የሚለውን ትዕዛዝ ቢሰጥም እያንዳንዱን የአካሉን ብልት ለተጠራበት አገልግሎት ያስታጥቀዋል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስጦታ ወይም ስጦታዎች አሉት። ሁሉም አንድ ዓይነት ስጦታ አልተሰጠውም። አንዳንዶች ከሌሎች ያነሱ ይመስሉ ይሆናል፤ ግን እያንዳንዱ ብልት ለአካላችን ጠቃሚ እንደሆነ ሁሉ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ለክርስቶስ አካል ጠቃሚ ነው። ለቤተሰቡ ማለት ለቤተ ክርስቲያን እርዳታና ጥቅም ስጦታችንን በመጠቀም የማገልገል ኃላፊነት አለብን። አንዱ ሌላውን በፍቅር በማገልገል እንደ አንድ የክርስቶስ አካል በአንድነት መሥራት አለብን።

1. የመንፈስ ስጦታዎች ምንና ምን ናቸው?

ሀ. በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ሐዋርያት፤ ነቢያት፤ ወንጌላውያን፤ እረኞችና አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች እንደሆኑ ተዘርዝሯል።

ለ. ከመንፈስ ስጦታዎች ጥቂቶቹ በ1ኛ ቆሮ.12ና ሮሜ 12 ላይ ተዘርዝረዋል። እነርሱም፡- ጥበብን መናገር፤ እውቀትን መናገር፤ እምነት፤ የመፈወስ ስጦታ፤ ታምራት ማድረግ፤ ትንቢትን መናገር፤ መናፍስትን መለየት፤ በልዩ ዓይነት ልሳን መናገርና በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ናቸው። ምናልባት ስጦታዎቹ ሁሉ አልተዘረዘሩም ይሆናል። ስለዚህ ሰባት፤ ዘጠኝ ወይም አሥራ አንድ ስጦታዎች አሉ ብሎ መከራከር የማይገባ መከፋፈልን መፍጠር ነው። ብዙ ዓይነት ስጦታዎች እንዳሉ መገንዘብ እንችላለን። እያንዳንዱ አባል በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጥበት ከነዚህ ስጦታዎች ቢያንስ አንዱ ተሰጥቶታል። መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ እንደ ፈቃዱ ይሰጣል። በነዚህ ስጦታዎች የመጠቀም ግዴታ አለብን።

2. አማኞች ስጦታዎች የተሰጡአቸው ለምንድን ነው? ኤፌ.4፡12-14።

ሀ. ስጦታዎቹ የተሰጡት የእግዚአብሔርን አካል ለማነጽ ነው።

ለ. ስጦታዎቹ የተሰጡት አማኞችን ለአገልግሎት ለማስታጠቅ ነው።

3. ስጦታዎቹ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ ውጤታቸው ምንድን ነው? ኤፌ.4፡13-16።

ሀ. በኅብረት መሥራት እንድንችል በእምነታችን መሠረት አንድነት ይሰጡናል።

ለ. መንፈሳዊ ዕድገት የሚሰጠንን እግዚአብሔርን የማወቃችንን ችሎታ ያዳብራሉ።

ሐ. ይበልጥ ክርስቶስን እንድንመስል ያደርጉናል።

መ. በሐሰት ትምህርት እንዳንሳሳት ይረዱናል።

ሠ. ለቤተ ክርስቲያን ፍቅርና ዕድገት ያመጣል ያገኙላታል።

4. ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን መሥራት ያለባቸው እንዴት ነው? አንዱ ሌላውን በመደገፍ እንደ አንድ አካል በኅብረትና የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን ክርስቶስን በመታዘዝ መሥራት አለባቸው።

## ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ስጦታዎችን የሚቀበል ማን ነው?
2. እያንዳንዱ አባል መቀበል ያለበትን ስጦታ የሚወስነው ማን ነው?
3. የመንፈስ ስጦታዎች የተሰጡት ለምንድን ነው?
4. የአባላቱ ስጦታዎች ሁሉ ቢሠሩ ውጤቱ ምንድን ነው?
5. ስጦታዎቹ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠናክሩት እንዴት ነው?

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር የትንቢት፥ የመስበክና የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣል። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ትምህርት ሲፈልጉ ሌሎች ደግሞ እረኛ ወይም ወንጌላውያን ይፈልጉ ይሆናል። በጥንት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያትንና ወንጌላውያንን እንደመራ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን እንደስጦታው ወደ ተገቢው አገልግሎት ይመራዋል፤ የሐዋ.16፡7-8፤ 8፡26 እና 29።

በቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ አባል ጥቂት ተሰጥኦ አለው፤ ይህንንም ስጦታ እንዲጠቀምበት ከጌታ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ስጦታዎቻችንን በታማኝነት

ስንገለገልባቸው ጌታ ሌላ ስጦታን ሊጨምርልን ወይም ሌሎች ስጦታዎች እንዳሉን ልንረዳ እንችል ይሆናል። ምንም ዓይነት ስጦታ ቢኖረን አንዱ ሌላውን በእምነት ለማነፅ በቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ መዋል አለበት። ስብከት ቢሆን ወይም ሌላ አነስተኛ አገልግሎት በስጦታችን አንዱ ሌላውን ለማገልገል ባለን ፍላጎት መጠን ይፈረድብናል።

ቤተ ክርስቲያኖቻችን የእያንዳንዱን አባል ስጦታዎች ይጠቀሙበታል? የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት እንዴት እንደሚጠቀሙባቸውና ወዴትስ እንደሚልኳቸው የእግዚአብሔርን ምሪት ይሻሉ? የሐዋ.13፡1-3።

# ተጨማሪ መግለጫዎች

የመንፈስ ስጦታዎች፡- 1ኛ ቆሮ.12፡1-11፤ 27-31፤ ሮሜ 12፡4-8፤ ኤፌ.4፡11-13።

ከሁሉም የበለጡ ስጦታዎች፡- 1ኛ ቆሮ.12፡31፤ 13፡13፤ 14፡1-4።

በአንድ አካል ውስጥ አገልግሎት የሚሠጡ ስጦታዎች፡- 1ኛ ቆሮ.12፡12-27።

# ጥናት ሰባት

# ጥምቀት (ሮሜ 6፡1-11)

## የጥናቱ ዓላማ

የአማኞች ጥምቀት ምን እንደሆነና በሕይወታችንም ውስጥ በትክክል መተርጎሙን ወይም አለመተርጎሙን እንድንገነዘብ ነው።

## መግቢያ

ጌታችን ትዕዛዙን እንዲያው በዘፈቀደ አልሰጠንም፤ ለትዕዛዙ ሁሉ ዓላማ አለው። ጌታ ሁለቱን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ያዘዘው ሕዝቡን ስለ ሁለት ታላላቅ እውነቶች ለማስታወስ ነበር። እነዚህም በጌታ እራት የሚታወሰው የመስቀል ሞቱና በጥምቀት የሚታወሰው ድል አድራጊው ትንሣኤው ናቸው።

*1.* የጥምቀት አጀማመር፡-

ሥነ ሥርዓቱ በኢየሱስ አልተጀመረም። ወደ ይሁዳነት የተለወጡ አሕዛብ ለመንፃታቸው ምልክት እንዲሆን ይጠመቁ ነበር። በመጥምቁ ዮሐንስ አማካይነት ለመጠመቅ የፈለጉት ሰዎች ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ንስሐ መግባት ነበረባቸው፤ ማቴ.3፡6፥ 11።

*2.* የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት፡-

የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ነበር፤ ማር.1፡4። ይህም ሰዎቹ ለኃጢአታቸው ማዘናቸውን ለማሳየት ይጠቀሙበት ነበር። ጥምቀቱ አዲሱን ሕይወት ለመኖር የሚያስችላቸው ኃይል አላስገኘላቸውም። ይህ ግን የተቻለው በመንፈስ ቅዱስ ባጠመቀው በክርስቶስ ብቻ ነበር፤ ዮሐ.1፡29-34።

*3.* የኢየሱስ ጥምቀት፡-

ኢየሱስ የተጠመቀው ለኃጢአት ንስሐ አልነበረም፤ እርሱ ምንም ኃጢአት አላደረገም፤ 1ኛ ጴጥ.2፡21-22።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ ለመፈፀም ነበር፤ ስለዚህ ለዮሐንስም ጥምቀት ታዛዥ ሆነ፤ ማቴ. 3፡13-17፤ መዝ.39፡7-8።

ሀ. ኢየሱስ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ተጠመቀ። የአብን ፈቃድ ለመፈጸም መጣ፤ ማቴ.3፡15፤ ዕብ.10፡7። ፍፁም የሆነውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለመፈጸም መጣ፤ ዮሐ.4፡34።

ለ. ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለማረጋገጥ ተጠመቀ፤ ዮሐ1፡33። ራሱን ከኃጢአተኞች ጋር ለማስተካከል ይህንን ፈፀመ፤ 1ኛ ቆሮ.10፡2፤ ፊልጵ.2፡5-7።

ሐ. ኢየሱስ በጥምቀቱ ለደቀ መዛሙርቱ ምሳሌ ሆኗቸዋል፤ ማቴ.16፡24፤ ፊልጵ.2፡4-8፤ 1ኛ ጴጥ.2፡21።

4. የአማኞች ጥምቀት፡-

ሀ. ጥምቀት በክርስቶስ የታዘዘ ነበር፤ ማቴ.28፡19። አንድ ሰው ካመነ በኋላ የሚጠመቀው ኢየሱስ ስላዘዘ ነው። አንድ ሰው አምኖ ሊጠመቅ አይችል ይሆናል፤ ለምሳሌ በመስቀል ላይ ሳለ ጌታን ያመነው ወንበዴ የመጠመቅ ዕድል አላገኘም ነበር፤ ሉቃ.23፡39-44።

ለ. ጥምቀት ከእምነት ቀጥሎ የሚደረግ ነው።

1. በበዓለ አምሳ ቀን ጴጥሮስ «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» በማለት ለአይሁድ ሰብኮላቸዋል፤ የሐዋ.2፡37-42።
2. ፊልጶስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰበከላቸው ስብከት ያመኑት ሰዎች ተጠምቀዋል፤ የሐዋ.8፡12።
3. የሐዋ. 26-39 ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ካመነ በኋላ ልጠመቅ በማለት ጥያቄ አቅርቧል፤ ፊልጶስም ደግሞ አጥምቆታል፤ የሐዋ.8፡26-39።
4. ሐዋርያው ጳውሎስ ካመነ በኋላ ተጠምቋል፤ የሐዋ.9፡1-19።
5. የፊልጵስዩስ ወህኒ ቤት ጠባቂና ቤተሰቡ ካመኑ በኋላ ተጠምቀዋል፤ የሐዋ.16፡25-34።
6. የምኩራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስም ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር በጌታ አምኖ ተጠምቋል፤ የሐዋ.18፡8።

ሐ. የአማኞች ጥምቀት ትርጉም፤ ሮሜ 6፡1-11፡-

1. ጥምቀት ከጋብቻ ቀለበት ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም፤ ስለዚህ ቀደም ተብሎ የተፈጸመውን ነገር የሚጠቁም ነው።

ሀ. በመንፈስ ቅዱስ የተለወጠ አዲስ ሕይወት መኖሩን ያመለክታል፤ ሮሜ 6፡4፥ 11።

ለ. የመለወጥ መታሰቢያና የአዲስ ኪዳን ምልክት ነው፤ ሮሜ 6፡3፥ 6።

ሐ. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለትም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መተባበር ማለት ነው።

2. ጥምቀት አያጸድቅም ወይም ከኃጢአት አያድንም።

ሀ. ማር.16፡16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል ይላል። ስለዚህ ፍርድን የሚያስከትለው አለመጠመቅ ሳይሆን አለማመን ነው።

ሰ. «በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ!» የሐዋ.16፡30-31። የወህኒ ቤት ጠባቂው ካመነ በኋላ ተጠምቋል።

ሐ. ኢየሱስም በመስቀል ላይ ሳለ ንስሐ ለገባው ወንበዴ እንዲህ አለው፡- «እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ።» ወንበዴው አመነ እንጂ መጠመቅ አልቻለም፤ ሉቃ.23፡43።

## ጥያቄዎች

1. የአማኞች ጥምቀት ዓላማ ምንድን ነው?
2. ጥምቀት የማያጸድቅ ወይም ከኃጢአት የማያድን መሆኑን የሚያስረዱ ሁለት ጥቅሶች ጥቀሱ።
3. ኢየሱስ የተጠመቀው ለምን ነበር?

## ማጠቃለያ

ጥምቀት የኢየሱስን ሞት፥ መቀበርና ትንሣኤውን የሚያሳይ ሥዕል ነው። ክርስቲያን የጥምቀትን ሥርዓት በመፈጸም እግዚአብሔርን ሲታዘዝ ራሱን ከክርስቶስና ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር አንድ ማድረጉ ነው።

## ተጨማሪ ጥቅሶች

ጥምቀት የክርስቶስ ትዕዛዝ ነው፤ ማር.16፡16፤ የሐዋ.2፡38፥ 41፤ 8፡36-40፤ 10፡47-48።

መጠመቅ - ማቴ.3፡6፥ 16፤ የሐዋ.8፡38-39፤ ሮሜ 6፡4-5።

የአዲስ ኪዳን የጥምቀት ምሳሌዎች - የሐዋ.2፡42፥ 46፤ 20፡7፥ 11፤ 1ኛ ቆሮ.10፡21፤ 11፡20።

# ጥናት ስምንት

# የጌታ እራት (1ኛ ቆሮ.11፡23-31)

### የጥናቱ ዓላማ

የጌታ እራትን ዓላማ በጥልቅ እንድንረዳ እና ከመውሰዳችንም በፊት ራሳችንን በመፈተን በአክብሮትና በምሥጋና እንድናደርገው ነው።

## መግቢያ

በመጨረሻው ምሽት ኢየሱስ ለመጨረሻው እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተገናኘ። በማዕድ ተቀምጠውም ሳሉ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንጀራና ወይን በመስጠት ወደፊትም ይህን ለመታሰቢያው እንዲያደርጉት አዟቸዋል፤ ማቴ.26፡26-29።

1. የጌታ እራት ትርጉም፤ 1ኛ ቆሮ.11፡23-32።

የጌታ እራት ለመታሰቢያ የሚደረግ ነው። ኢየሱስ «ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» ብሏል። የጌታ ሞትና ትንሣኤ መታሰቢያ ነው።

- እንጀራው፡- የኃጢአት መስዋዕት ለመሆን ብቃት ያለውንና ፍፁም የሆነውን ሕይወቱን ይመስላል፤ 1ኛ ጴጥ.2፡24።

- ወይኑ ደግሞ ለኃጢአት ሥርየት የፈሰሰውን ደሙን ያመለክታል።

2. የጌታ እራት ዓላማ፡-

ሀ. የጌታ እራት የወንጌል መሠረት የሆነውን ለኃጢአት ሥርየት የተሰቀለው ሥጋውንና የፈሰሰው ደሙን ያመለክታል፤ 1ኛ ቆሮ.11፡26።

ለ. ይህንንም ጌታ እስኪመጣ ድረስ እንድናደርገው ታዞናል፤ የጌታ እራት የጌታን ዳግም ምፅዓት በትጋት እንድንጠባበቅ ያደርገናል፤ 1ኛ ቆሮ.11፡26።

ሐ. የጌታ እራት በክርስቶስ አካል ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር አንድ መሆኑን ያስገነዝበናል፤ 1ኛ ቆሮ.10፡17።

3. መደረግ ያለበት በየስንት ጊዜ ነው?

አንዳንዶች በየሳምንቱ፥ በየወሩ ሲያደርጉ ሌሎች ደግሞ በሦስት ወር ወይም በዓመት አንድ ጊዜ ያደርጋሉ። አንዳንዶች በጥዋቱ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ሲያደርጉት ሌሎች ደግሞ በማታው ስብሰባ ያደርጉታል። ከበዓለ አምሳ በኋላ ምዕመናን የጌታን እራት በየቀኑ ሳያደርጉት አልቀሩም፤ የሐዋ.2፡46። በጢሮአዳ ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን አድርገዋል፤ የሐዋ.20፡7። በየስንት ጊዜው መደረግ እንዳለበት የሚያመለክት ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ የለም።

4. ለጌታ እራት መደረግ የሚገባው ጥንቃቄ፡-

ሀ. በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ላሉት ማለትም ለክርስቲያኖች የሚሆን ማስታወሻ ነው።

ለ. ያልተናዘዝነው ኃጢአት ካለ የጌታን እራት መሳተፍ የለብንም። ከዚህ የተነሳ በቆሮንቶስ የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ተቀጥተዋል፤ እንዲያውም ጥቂቶች ሞተዋል፤ 1ኛ ቆሮ.11፡17-34።

ሐ. የጌታ እራትን ስንሳተፍ ልባችንን በመመርመር በአክብሮት እና በምስጋና መሆን አለበት። የጌታን እራት መሳተፍ አያድንም ወይም አያጸድቅም፤ ኤፌ.2፡8-9።

## ጥያቄዎች

1. የጌታን እራት የጀመረው ማንና መቼ ነበር?
2. የጌታ እራት ዓላማ ምንድን ነው?
3. የጌታን እራት ለሚሳተፉ ሰዎች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

የጌታ እራት የእሥራኤላውያን ከግብፅ አገር መውጣት መታሰቢያ የሆነውን የፋሲካን በዓል ተክቷል። ይህ አዲስ መታሰቢያ የሆነው የጌታ እራት አዲስና ዘላለማዊ የሆነው ኪዳን ማስታወሻ ነው። የጌታ እራት የክርስቶስን ሞትና ለእኛም መሞቱን ያስገነዝባል። በሞቱና በትንሣኤው ከእርሱ ጋር አንድ መሆናችንንም ያስታውሰናል። ይህም ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ መደረግ አለበት።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ኢየሱስ የጌታን እራት ደነገገ፤ ማር.14፡22-25፤ ሉቃ.22፡17-20፤ 1ኛቆሮ.11፡23-26።

የጌታ እራት በጥንት አብያተ ክርስቲያናት፡- የሐዋ.20፡7፤ 27፡35ና 2፡42፥ 46።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጌታን እራት በተገቢው መንገድ አላደረገችም፤ 1ኛ ቆሮ.11፡20-22፥33-34።

# ጥናት ዘጠኝ

# የቤተ ክርስቲያን ተቋም (1ኛ ጢሞ.3፡1-16)

## የጥናቱ ዓላማ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተገለፀው መሠረት የቤተ ክርስቲያንን ድርጅታዊ መዋቅር በተለይም የጉባኤው ኃላፊነት ምን እንደሆነ ለመረዳት እንድንችል ነው።

## መግቢያ

ኢየሱስ በማቴ.20፡25-27 «ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን» በማለት ቤተ ክርስቲያን እንዴት መተዳደር እንዳለባት ደንግጓል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ማለት ተገልጋይ ሳይሆን አገልጋይ ማለት ነው።

## ሐዋርያት

አዲሱ ኅብረት የተቀነባበረው እንዴት እንደሆነ አዲስ ኪዳን ትክክለኛ የሆነ ዝርዝር አይሰጠንም። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጥቂቶቹን መርጦ የተለየ ኃላፊነት እንደሰጣቸው እናውቃለን። እነዚህም ሐዋርያት ነበሩ። የአሥራ ሁለቱ የተለየ አስተዋጽኦ እጥፍ ድርብ ሆኖ ይታያል።

1. የትንሣኤው ታማኝ ምስክሮች ለመሆን ተጠርተዋል። ከእነርሱ በኋላ «ከኢየሱስ ጋር ሦስት ዓመት ኖርን፤ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ዓይተነዋል» ያለ ሌላ ቡድን ፈጽሞ የለም።
2. የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ለመሆን ተጠርተዋል። ይህ ሥልጣን የተሰጠው ለመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ሐዋርያት ብቻ ነበር። ሌሎች ይህ ሥልጣን አልነበራቸውም።

እነዚህ ሐዋርያት ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያገለግሉ ተጨማሪ ኃላፊነቶች ተቀብለው ነበር።

1. አሕዛብን ሁሉ ማስተማር ነበረባቸው፤ ማቴ.28፡18-20፤ የሐዋ.1፡8።
2. የእግዚአብሔርን ሰዎች ማስተዳደርና በእነርሱም ላይ መፍረድ ነበረባቸው፤ ማቴ.16፡16-19፤ 18፡18። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትምህርተ ክርስትና ተሰጥቷቸው ነበር፤ ማቴ. 16፡16-18።
3. እግዚአብሔር የሚሰጠው የኃጢአት ይቅርታ በክርስቶስ በኩል ብቻ መሆኑን በማስተማርና መንፈሱ የዛለበትን ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ፥ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ያልሆነውን የሚያስወግዱበት እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሥነ ሥርዓት ተሰጥቷቸው ነበር ማቴ.16፡19፤ 18፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 5።

በአሁኑ ጊዜ ሐዋርያት እነማን ናቸው? ኤፌ.4፡11። እንደ መጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ሐዋርያት ባይሆኑም እንኳ በአሁኑም ዘመን ከቀደሙት ሐዋርያት ጋር የሚመሳሰል ተግባር ያላቸው ሰዎች ይገኛሉ።

1. ወንጌል ላልደረሰበት በታ ሁሉ ክርስቶስ ሕያው መሆኑን መስካሪዎች ናቸው።

2. ከመካከላቸው ሽማግሌዎች እስኪመረጡ ድረስ አዲስ አማኞችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

እንዲት አዲስ ቤ.ክ. ስትመሠረት ራሷን መርዳት እስከምትችልበት ጊዜ ድረስ በዚያ ሥፍራ ጊታ ሐዋርያ ይመድባል።

## ጉባኤ

የሚያምኑ ሁሉ የክርስቶስ አካል ብልቶች በመሆናቸው እንደ አንድ አካል ብልቶች መሥራት አለባቸው። ጳውሎስ የመጀመሪያዎቹን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደሾመ የሐዋ. ምዕ. 14 ይገልጻል፤ በኋላ ግን የጉባኤው ቁጥር እየጨመረና እየጎለመሱም ሲሄዱ የራሳቸውን መሪዎች እንደመረጡ እናነባለን። ጳውሎስ አብዛኛዎቹን ደብዳቤዎቹን የጻፈው ለሽማግሌዎች ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነበር። ጳውሎስ በቤ.ክ. ለሚቀርበው ለትምህርቱና ለሥነ ምግባር ሁሉም ኃላፊነት እንዲሰማቸው ይፈልጋል። ይህንንም በማቴ. 18 እና 1ኛ ቆሮ. ምዕ. 5 እናነባለን። ሁሉም በቤተ ክርስቲያን ተሳትፎ እንዲኖራቸው መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ስጦታዎችን ሰጥቷል፤ ኤፌ. 4፡12-14፤ 1ኛ ቆር.12፡1-12፤ ሮሜ 12፡5-9።

ወንጌልን ማሰማትና መምሪያ መስጠት ከጉባኤው መካከል የጥቂት ተመራጮች መብት ብቻ ሳይሆን የአማኞች ሁሉ ኃላፊነት ነው።

## ዲያቆናት

በሐዋርያት ዘመን በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ ሁለት ዓይነት ሠራተኞች የነበሩ ይመስላል። እነርሱም፡-

1. ሰባኪና አስተማሪ የነበሩት ሽማግሌዎች

2. በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ አቀነባባሪና ረዳት የነበሩት ዲያቆናት ናቸው።

የኢየሩሳሌም ጉባኤ የመረጣቸው ሰዎች ዲያቆናት ተብለው አልተጠሩም፤ የሐዋ.6። ነገር ግን በተለያየ መንገድ አቀነባባሪና ረዳት ስለነበሩ ዲያቆናት ተብለው ቢጠሩ ስሕተት አይደለም።በ1ኛጢሞ.3፡8-13 ውስጥ ዲያቆናት ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ተጠቅሷል። እነዚህ መመሪያዎች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው በዲያቆናት ምርጫ ጊዜ በጥንቃቄ በተግባር ላይ መዋል አለባቸው።

ዲያቆናት በሌሉባቸው አብያተ ክርስቲያናት ቢያንስ ሦስት ነገሮች ይፈጠራሉ፡-

1. ሽማግሌዎች ሥራ ስለሚበዛባቸው ስብከቱና ትምህርቱ ችላ ይባላል፤

2. ሽማግሌዎች ገንዘብ ነክ የሆኑ ሥራዎችንም ስለሚሠሩ ሌላው ሥራቸው ይበደላል፤

3. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ ይሆናል።

# ሽማግሌዎችና ጳጳሳት

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህ ሁለቱ አንድ ናቸው። ምናልባት በእነዚህ ነገሮች ላይ ለሚፈጠሩት ጥያቄዎች መረጋገጫ እንዲሆናችሁ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ:- የሐዋ.13፡1-2፣ 14፡23፣ 1ኛ ጢሞ.3፡1-7። ሽማግሌዎች ለሐዋርያት የተሰጡትን ሦስት ሥራዎች ማከናወን አለባቸው። እነርሱም:-

1. ማስተማርና ወንጌልን ማሰራጨት፥
2. ትምህርተ ክርስትና የተሳሳተ ትርጉም እንዳይሰጠውና በተግባርም መተርጎሙን ተከታትሎ መመልከትና
3. ሥነ ምግባርን መቆጣጠር ናቸው።

አንድ ሽማግሌ ከሌላው የሚበልጥ ቦታ እንደሚሰጠው የታወቀው ከሐዋርያት ዘመን አንድ መቶ ዓመታት በኋላ ነው።

በመጀመሪያ በሐዋርያት በተሾሙ ጊዜ ኃላፊነታቸው ለእነርሱ ነበር። በኋላ ግን ሽማግሌዎቹ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት መሥራታቸውን ለሚታዘቡ የጉባኤው አባላት ኃላፊዎች ነበሩ። ከሁሉም በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

# እረኞች

በሐዋርያት ዘመን ይህ የተለየ ኃላፊነት አልነበረም። ሽማግሌዎቹ ሁሉ መንጋውን የሚጠብቁ እረኞች ነበሩ።

ጉባኤው የማስተማር ወይም የመስበክ ስጦታ ያለውን አንድ ሽማግሌ ሊመርጥ ቢፈልግ አዲስ ኪዳን አይከለክልም። እረኛ የሚለው ቃል የተገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚከተሉት ቦታዎች ከተጠቀሰው ግሥ ነው፤ ማቴ.2፡6፤ ሉቃ.17፡7፤ ዮሐ.21፡16፤ የሐዋ.20፡28፤ 1ኛ ቆሮ.9፡7፤ 1ኛ ጴጥ.5፡2፤ ይሁዳ 12፤ ራዕይ 2፡27፤ 7፡17፤ 12፡5፤ 19፡15።

# ወንጌላውያን

በስብከት ለማገልገል የግል ሥራቸውን የተዉ የአዲስ ኪዳን ሠራተኞች እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ የሐዋ.13፡1-3 ተመልከቱ። ለአገልግሎት ሳይወጡ በፊት በቤተ ክርስቲያን ሌላ ሥራ እንደነበራቸው እንገነዘባለን። ለምሳሌ ከተመረጡት ሰባት አገልጋዮች አንደኛ ፊልጶስ በኋላ ወንጌላዊ ሆኗል፤ የሐዋ. 6፡1-6፤ 8፡4-8፥ 26-40፤ 21፡8።

ጢሞቴዎስ የወንጌላዊነት ሥራ እንዲሠራ ጳውሎስ በጥብቅ አሳስቦታል፤ 2ኛ ጢሞ.4፡5።

ጳውሎስ በኤፌ.4፡11 ባቀረበው የሹማምንት ዝርዝር ውስጥ ወንጌላውያን ከነቢያት ቀጥለው የተጠቀሱት ናቸው። እነዚህም የምሥራቹን ተናጋሪዎች ወይም ወንጌልን ሰባኪዎች ናቸው። ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው። «የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ» የሚለው በስደት ተበታትነው የነበሩ አማኞችን ማለቱ ነው፤ የሐዋ.8፡4።

ሆኖም አንዳንዶች ስጦታ ስላላቸው ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት ተጠርተዋል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ኅብረት፥ ዕድገትና ጉልምስና እንዳይደናቀፍ ለማድረግ ወንጌላውያን ሽማግሌዎች ሲሾሙ ወዲያውኑ እንደ ነቢያት ወንጌል ላልደረሳቸው ለመስበክና ለማስተማር መንቀሳቀስ አለባቸው።

ሐዋርያት ወንጌላውያን ቢሆኑም ወንጌላውያን ሁሉ ሐዋርያት አይደሉም። እረኛ ግን ወንጌላዊም መሆን ሳይችል አይቀርም።

## ነቢያት

እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት ከጠራቸው ሰዎች መካከል ነቢያት የሚባሉ ጥቂት ወንዶችና ሴቶች ነበሩበት። ነቢይ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገር ሲሆን የሚናገረው ስለ ወደፊቱ ብቻ ነው ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው። ነቢይ ስለ አላፊው፥ ስለአሁንና ስለ ወደፊት መናገር ይችላል። በአዲስ ኪዳን ነቢይ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር እኩል ነበር። ሐሰተኛ ሐዋርያት፥ ወንጌላውያንና ነቢያትም ነበሩ። የነቢያቱ ቃል መለኮታዊ መገለጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ጉባኤው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ መሆኑን ማመሳከር አለበት።

የእነዚህና በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የሌሎች አገልጋዮች ዓላማ ጉባኤውን ለማገልገል ነው። ትምህርታቸው በምግባራቸው ማለትም «በፍሬያቸው» መረጋገጥ አለበት። ይህ ጥቅስ በተለይ ክርስቲያን ሠራተኞችን እንጂ ሌሎች ክርስቲያኖችን የማይመለከት መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ እረኛ፥ ሽማግሌ፥ ወንጌላዊ ወይም ነቢይ ሐሰተኛ ነው፤ የሚሰብከውንም በተግባሩ ይክደዋል።

## ጥያቄዎች

1. የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት የተለዩ የሆኑት በምን ነበር?
2. አንድ ሐዋርያ ወይም ወንጌላዊ ጉባኤው የራሱን ሽማግሌዎች እንዲመርጥ ባይፈቅድለት ውጤቱ ምን ይሆናል?
3. ዲያቆናትና ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ያስፈለጉት ለምንድን ነው?
4. ለሽማግሌዎች የተሰጡት ሦስት ተግባራት ምንና ምን ናቸው?
5. በአንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን መምረጥ ያለበት ማን ነው?
6. ሽማግሌዎቹ በአዲስ ኪዳን መመሪያዎች መሠረት መሥራታቸውን ማረጋገጥ የሚገባው ማን ነው?

## ማጠቃለያ

ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ስለ ቤተ ክርስቲያን ተቋም አስተዳደር የተገኙ አምስት አጠቃላይ መሠረታዊ መመሪያዎች፡-

1. ሥልጣን ሁሉ የክርስቶስ ስለሆነ በስሙና በእርሱ መንፈስ አማካይነት በተግባር ላይ መዋል አለበት።
2. የክርስቶስ ትሕትና ለክርስትና አገልግሎት ምሳሌ ነው፤ ማቴ. 20፡26-28።
3. ቤተ ክርስቲያንን የመቆጣጠር ተግባር ለጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለጉባኤውም ተሰጥቷል።

4. ማስተማርና ማስተዳደር የተያያዙ ናቸው፤ 1ኛ ተሰ.5፡12።

5. አስተዳዳሪዎች ቃሉን የሚሰብኩትን እንዲረዷቸው ያስፈልጋል፤ የሐዋ.6፡2-3።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

የሽማግሌነት መመዘኛ:- ቲቶ 1፡4-16።

የጉባኤው መመዘኛዎች:- ቲቶ 2፡1-8፤ ሮሜ 12፡9-21፤ 1ኛ ተሰ.5፡12-23።

# መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚያስተምረው ትምህርት

## ጥናት አሥር

## ጋብቻ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው (ዘፍ.1፡26-28፤ 2፡18-24)

**የጥናቱ ዓላማ**

ጋብቻ በእግዚአብሔር የታዘዘ ተቋም መሆኑንና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድም መፈጸም እንዳለበት ለማስረዳት ነው።

## መግቢያ

እግዚአብሔር ጋብቻን በመጀመሪያ ያቀደው ለባልና ሚስት ደስታ እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር የሚያቅደው ሁሉ መልካም ነው። ሆኖም ጋብቻ መልካምና አስደሳች የሚሆነው እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ ሲፈጸም ነው።

1. የጋብቻ ተቋም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነበር።
   - ሀ. ክርስቲያኖች ጋብቻ የኅብረተሰቡን ቁጥር ለመጨመርና ሰላምን ለማግኘት የሚፈጸም ማኅበራዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ያምናሉ።
   - ለ. ወንድና ሴት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር አምሳል ነው፤ ዘፍ.1፡26-27።
   - ሐ. ወንድና ሴት አብረው ምድርን እንዲቆጣጠሩ መብት ተሰጥቷቸዋል፤ ዘፍ.1፡28።
   - መ. ባልና ሚስት ልጅ በመውለድ ምድርን እንዲሞሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ዘፍ.1፡28።
2. ጋብቻ መልካም ነው፤ ዕብ.13፡4።
   - ሀ. አዳም ረዳት አስፈልጎት ስለነበር እግዚአብሔር ሔዋንን ሲሰጠው ተደስቷል፤ ዘፍ.2፡23።
   - ለ. እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ከሌሎች ጋር በኅብረት ለመኖር እንዲችሉ አድርጎ ፈጥሯቸዋል።
   - ሐ. ወንዶችና ሴቶች በሕጋዊ ጋብቻ ሳይተሳሰሩ በአንድነት እንዲኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፍም።
3. ጋብቻ የተባረከ እንዲሆን በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት መፈፀም አለበት፤ ቆላ.3፡17-19፥ 23-25።
   - ሀ. የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ጋር ተጋብቶ እንዲኖር ነው፤ ዘፍ.2፡18፤ ማቴ.5፡32።
   - ለ. አማኞች ያላመኑትን ማግባት የለባቸውም፤ 2ኛ ቆሮ.6፡14።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ትዕዛዝ መስጠቱን የሚያመለክቱ ሁለት ጥቅሶች ጥቀሱ።
2. ጋብቻ ደስታ የሚገኝበትና የእግዚአብሔርም በረከት እንዳይለየው ምን ያስፈልገዋል?
3. አብዛኛውን ጊዜ ጋብቻ የማይባረክበትን ምክንያት ግለጹ።

## ማጠቃለያ

ጋብቻ ከተፈጥሮ ሕግ የተገኘ ብቻ አይደለም። ጋብቻ ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ይህ ከፍተኛ መቀራረብ ያለበት ግንኙነት ፍሬያማ የሚሆነው እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት የትዳር ጓደኛሞች እርሱ የሰጣቸውን ኃላፊነት በትክክል ሲፈጽሙ ብቻ ነው።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

## የወንዶች ኃላፊነት፣ መዝ.8፡6-8፥

ጋብቻ ክቡር ነው፣ ምሳሌ 18፡22፣ 1ኛ ጢሞ.3፡12፣ 5፡14።

ጋብቻ እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት ምሳሌ ነው፣ ኢሳ54፡5፣ 62፡5፣ ኤር.3፡14፣ ማቴ.22፡2፣ 25፡10፣ ራዕይ 19፡7።

የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ኅብረት ከጋብቻ ኅብረት ጋር ይነጻጸራል፣ ኤፌ.5፡23፣ ቆላ.1፡18።

## ጥናት አሥራ አንድ

## በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ የባልና ሚስት የሥራ ድርሻ

## ኤፌ.5፡21-33፣ 6፡4

### የጥናቱ ዓላማ

ስለ ክርስቲያን ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን መሠረታዊ መመሪያዎች ተረድተን እንድንለማመዳቸው ነው።

## መግቢያ

እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱና አንድ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ፈጠረ። በክርስቶስ እኩል ናቸው፣ ነገር ግን በቤተሰብ ኑሮ ውስጥ የተለያዩ ድርሻዎች አሏቸው።

1. የባል ኃላፊነት፡-

ሀ. ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን እራስ እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነው፣ ኤፌ.5፡23።

ለ. ባል ሚስቱን መውደድ የሚገባው፡-

- ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳትና
- እንደ ገዛ ሥጋው መሆን አለበት፣ ኤፌ.5፡25-29።

ሐ. ሚስቱ ደካማ ፍጥረት ስለሆነች ከእርሷ ጋር በማስተዋል አብሮ መኖር አለበት፣ 1ኛ ጴጥ.3፡7።

መ. አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ኤፌ.5፡31።

2. የሚስት ኃላፊነት፡-

ሀ. ለጌታ እንደምትገዛ እንዲሁ ለባልዋ ትገዛ፤ ኤፌ.5፡22። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስት ለባልዋ ትገዛ፤ ኤፌ.5፡24።

ለ. ሚስት ባልዋን ትፍራ፤ ኤፌ.5፡33።

ሐ. ለባልዋ ረዳት ትሁን፤ ዘፍ.2፡18።

3. ባል ለሚስት ሚስቱ ደግሞ ለባልዋ ያለባት ኃላፊነት፡-

ሀ. በፍቅር ይኑሩ፤ ኤፌ.5፡1-2።

ለ. ለእያንዳንዳቸው በክርስቶስ ፍርሃት የተገዙ ይሁኑ፤ ኤፌ.5፡21።

ሐ. በፍቅር፤ በርህራሄና በትህትና በአንድ ልብ ይሁኑ፤ 1ኛ ጴጥ.3፡8።

4. የወላጆች የጋራ ኃላፊነት፡-

ሀ. ልጆቻቸውን በማፍቀር በጌታ ምክርና ተግሣጽ ማሳደግ ይኖርባቸዋል፤ ኤፌ.6፡4፤ 1ኛ ጢሞ.3፡4፤ ቲቶ 1፡6።

ለ. ለቤተሰባቸው ማሰብ አለባቸው፤ 1ኛ ጢሞ.5፡8፥ 14፤ ምሳሌ 31፡24፥ 27።

## ጥያቄዎች

1. የባል ኃላፊነት ምንድን ነው? ባሎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ኃላፊነት የሚዘነጉት እንዴት ነው?
2. ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር የሚነጻጸረው ከምን ጋር ነው?
3. የሚስት ኃላፊነት ምንድን ነው? ሚስቶች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ኃላፊነት የሚዘነጉት እንዴት ነው?
4. ሚስት ለባሏ ያላት አመለካከት ምን ዓይነት መሆን አለበት?
5. ሚስት ለባሏ የምታሳየው የመገዛት ባሕሪይ ከምን ጋር ይነጻጸራል?
6. ወላጆች ለልጆቻቸው ያለባቸው ኃላፊነት ምንድን ነው? ይህ የጋራ ኃላፊነት የሆነው ለምንድን ነው? አንዱ ኃላፊነቱን ቢዘነጋስ ምን ችግር ይፈጠራል?

## ማጠቃለያ

1. ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሰልጠንና ለመገሰጽ የማይስማሙና የማይተባበሩ ከሆነ በልጆቻቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ።
2. ባልና ሚስት ሁለቱም ኃላፊነታቸውን በመወጣት ታማኞች ከሆኑ ሌሎች ኃላፊነታቸውን በቀላሉ እንዲወጡ ይረዱዋቸዋል።
3. ከዚህ በታች የተሰጡትን ሁለት ዘመናዊ አስተሳሰቦች ተወያዩባቸው፡-

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት መጋባት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ዝም ብለን አብረን እንኑር የሚሉ አሉ።

ለ. ያገቡ ሰዎች መውለድ ይገባቸዋል? ልጆች አንፈልግም ብለው ቢስማሙስ?

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሚስት ደግሞ ለባልዋ የሚገባውን ታድርግ፤ 1ኛ ቆሮ.7፡2-5።

ሚስቶች ለባሎቻቸው ይገዙ፤ 1ኛ ጴጥ.3፡1-2፤ ቆላ3፡18። ባሎች ሚስቶቻቸውን ይውደዱ፤ ቆላ 3፡19፤ 1ኛ ጴጥ.3፡7። የወላጆች የጋራ ኃላፊነት፤ ቆላ3፡17፥ 21፤ 1ኛ ጴጥ.3፡8-9።

ሚስቶች ባሎቻቸውን ይርዱ፤ ምሳ31፡10-31። ወላጆች ልጆቻቸውን በጌታ ትዕዛዝ መሠረት ያሳድጉ፤ ምሳ.13፡34፤ 22፡6፥ 15፤ 19፡18፤ ቲቶ 2፡9።

## ጥናት አሥራ ሁለት

## የክርስቲያን ጋብቻ መምሪያ (ማቴ.19፡1-12)

### የጥናቱ ዓላማ

እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለውን ዕቅድ ያበላሸው ኃጢአት መሆኑን እንድንገነዘብና የክርስቲያን ጋብቻ ከሌሎቹ የጋብቻ ዓይነቶች የተለየ መሆኑን እንድናስተውል ነው።

## መግቢያ

እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ልዩ መመሪያ ሰጥቷል። የጋብቻ መመሪያው በትክክል በተግባር ላይ ካልዋለ ጋብቻው የሚፈርስ መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል። የቤተሰብ መፍረስ ደግሞ የአገር ድክመት ያስከትላል።

1. ክርስቲያኖች የማያምኑትን ማግባት የለባቸውም፤ 2ኛ ቆሮ.6፡14።
   ሀ. ያላመነ የትዳር ጓደኛ ያመነውን ያስከዳል።
   ለ. ከተጋቡት መካከል አንደኛው ቢያምን ያላመነውን መፍታት የለበትም፤ 1ኛ ቆሮ.7፡12-16።
2. በዝሙት ምክንያት ካልሆነ ክርስቲያኖች መፋታት የለባቸውም፤ ማቴ.5፡32፤ 19፡9።

አንዳንድ ምሁራን ጥፋት የሌለው ወገን እንደገና ሊጋባ ይችላል ብለው ያስተምራሉ፤ ማቴ. 19፡9፤ 1ኛ ቆሮ.7፡39። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዳግም ጋብቻን በግልጽ የሚደግፍ ሐሳብ የለም፤ ነገር ግን በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ከመጨመር «አንድ ገመድ ቢበጠስ የብጣሾቹን ጫፍ አስቀያሚ በሆነ ቋጠሮ እንኳ ማያያዙ ቢያንስ ሁለቱም እንዳይጠፉ ያደርጋል» እንደሚባለው ማድረግ ይሻላል። ሆኖም «ጌታ ያጣመረውን ማንም አይለይ» ተብሏል።

3. መጽሐፍ ቅዱስ ሳይጋቡ አብሮ መኖርን ይቃወማል።
4. እግዚአብሔር አንዳንዶች ያለ ጋብቻ እንዲኖሩ ይፈቅድላቸዋል፤ ማቴ.19፡12። እግዚአብሔር የወንድና የሴትን ፍጥረትና መጣመር መልካም እንደሆነ አየ፤ ዘፍ.1፡31።

ኃጢአት የጋብቻ ደስታና ስቃይ አስከትሏል። በኤደን ገነት ብቸኝነት አልነበረም። ኃጢአት ብዙ የማይጥሙ ጋብቻዎችን እንዳስከተለ ሁሉ ብቸኝነትም ብዙውን ጊዜ የኃጢአት ውጤት ነው። ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሳያገቡ ይቀሩ ይሆናል። እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች እንዲያገለግሉት በጋብቻ ወጥመድ እንዳይታሰሩ ይከለክላቸዋል።

እግዚአብሔር ንጉሥ ነው። ጋብቻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ሆኖም ይህንን ስጦታ ላይሰጥ ይችላል። ለክርስቶስ ብለው ሁለንተናቸውን በማስገዛት ይህንን ስጦታ የተዉ በጌታ ይረካሉ።

## ጥያቄዎች

1. አማኞች ያላመኑትን ማግባት የሌለባቸው ለምንድን ነው?
2. ለሕጋዊ መፋታት መንስኤ ሊሆን የሚችለው ብቸኛ ምክንያት ምንድን ነው?
3. እግዚአብሔር አንዳንዶች ሳያገቡ እንዲኖሩ የሚፈቅደው ለምንድን ነው?
4. ፍች የተፈቀደው ለምን ነበር?

## ማጠቃለያ

ሰው ይለወጣል፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይለወጥም። ሰው ኃጢአትን እያበዛ ሲሄድ የጋብቻና የፍች ችግሮች በመጨመራቸው ለሕይወት፥ ለቤተሰብና ለቤተ ክርስቲያን ጠንቅ እየሆኑ ነው። በክርስቲያኖች ሕይወት ግን ይህ ሊሆን አይገባውም። የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች ልንፈጽም የሚያስችለን ኃይል አለን። ዛሬ ዓለም፥ እንዲያውም ክርስቲያኖች ጭምር ፍችን እንደቀላል ነገር ቢወስዱትም እንኳ ቀላል ነገር አይደለም።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ክርስቲያኖች ያላመኑትን ማግባት የለባቸውም፤ ዘፍ.24፡3፤ 28፡1፤ ዘዳ.7፡3፤ ኢያ.23፡12፤ ሕዝ.9፡12፤ ነህ.13፡25።

ፍች፡- ማቴ.5፡31-32፤ ማር.10፡9፤ ሮሜ 7፡2፤ 1ኛ ቆሮ.7፡10-11፤ 8፡39።

ብቸኝነት፡- 1ኛ ቆሮ.7፡25፥ 26፥ 32-35፥ 40።

# መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት
# የሚያስተምረው ትምህርት
# ጥናት አሥራ ሦስት
## ጸሎት ምንድን ነው? (መዝ.120)

**የጥናቱ ዓላማ**

ስለ ጸሎት ምንነት ጠለቅ ያለ እውቀት እንድናገኝ ነው።

## መግቢያ

ልጆች ከወላጆቻቸው ጋራ መነጋገር እንደሚፈልጉ ሁሉ እንዲሁ የእግዚአብሔር ልጅ ከሰማያዊ አባቱ ጋር መነጋገር ተገቢ ነው። ልጆች በተለይም በችግር ወይም በአደጋ ጊዜ አባታቸው በቅርብ መሆኑን ማወቅ ይፈልጋሉ። ጸሎት እኛ ለእግዚአብሔር የምንናገረውና የምናቀርበው ልመና ብቻ ሳይሆን እርሱ እንዲናገረንና ለመስማትም ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው።

1. ጸሎት ማለት እርዳታ እንደሚያስፈልገን ማወቅ ማለት ነው፤ መዝ.120፡1-2።
   - ጸሎት ደካማነትን ማወቅ ማለት ነው፤ ይህም የመጀመሪያውና እርግጠኛው ለጸሎት የተዘጋጀ ልብ ምልክት ነው። ጸሎት ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን ከመግባቱ በፊት ብቻ ሳይሆን በክርስትና ዘመናችን ሁሉ ልናደርገው የሚገባ ነው።
   - ጸሎት ያለ ጌታ ምንም ልናደርግ አለመቻላችንን ማወቅ ማለት ነው፤ ዮሐ.15፡5።
   - ድካማችንን በትክክል ስንረዳ እርግጠኛ ጸሎት መጸለይ እንችላለን፤ ነገር ግን በመጨረሻ ወደ ጸሎት ከመቅረባችን በፊት የማንሞክረው ነገር የለም።
   - ብዙ ማራኪ ቃላትን እንለፈልፋለን፤ ነገር ግን ያለ እርዳታ ፍለጋ ወይም ደካማነት ስሜት ይህ እውነተኛ ጸሎት አይደለም።
2. ጸሎት እግዚአብሔር ምንጊዜም የማይተኛ አምላክ መሆኑን ማመን ማለት ነው፤ መዝ.120፡3።
   - ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ እምነታችንን ያመለክታል።
   - ያለ ማቋረጥ ስንቀርበው እምነታችን ይጨምራል።
   - እግዚአብሔር ከጊዜ ቁጥጥር ውጪ የሚኖር አምላክ መሆኑን ማመን አለብን፤ ዕብ.11፡6፤ መዝ.138፡7-10።
3. ጸሎት እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜ ሰምቶ ሊረዳን ዝግጁ መሆኑን ማወቅ ማለት ነው፤ መዝ.120፡4-6።
   - እግዚአብሔር ጸሎታችንን ለመስማት ሁልጊዜ ዝግጁ የሆነና የማያንቀላፋ አምላክ ነው። ሳንጠራው ይመልስልናል፤ ኢሳ.65፡24።
   - ክርስቶስ አይለወጥም፤ ዕብ.12፡8። እርሱ የሚፈልገው ወደ ሕይወታችን መግባት ብቻ ነው፤ ብንፈቅድለት ይገባል።

4. ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ኅብረት ምንም ዓይነት ውጫዊ ኃይል ሊለየን እንደማይችል ዋስትና ነው፤ መዝ.120፡7-8።

- ከእግዚአብሔር ፍቅር ማንም ሊለየን አይችልም፤ ሮሜ 8፡35-39።
- ጌታ የራሱ የሆኑትን ሁልጊዜ ይጠብቃቸዋል፤ 2ኛ ዜና 17፡9።
- ጌታ ሊጠብቀን ቃል ገብቶአል፤ ምሳሌ 3፡23፥ 26።
- ጌታ ከክንቱ ነገር ሁሉ ይጠብቀናል፤ መዝ.4፡2።

## ጥያቄዎች

1. ለጸሎታችን ውጤት ከማግኘታችን በፊት ደካማነትን የመረዳት ስሜት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
2. እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያለ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ጥቅስ ጥቀሱ።
3. ወደ እግዚአብሔር መቅረባችን እምነታችንን የሚያመለክተው ለምንድን ነው?
4. ያለ ማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ በእምነታችን ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

1. ጸሎት ከተራ ንግግር በላይ ነው። የልባችንና የሐሳባችን ዝንባሌ የሚያመለክት ነው።
2. ራሳችንን ለማሳመን ወይም ጥርጣሬን ለማስወገድ ራሳችንን ማስገደድ አያስፈልገንም፤ ለዚህ የሚያስፈልገን ወደ እግዚአብሔር ቀርበን ችግራችንን መናዘዝ ብቻ ነው።
3. የጸሎት መልስ ረዘም አድርገን ወይም ጋል ባለ መንፈስ በመጸለያችን ሳይሆን ልባችንን ለእግዚአብሔር ለመክፈት ባለን ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው።
4. እንድንጸልይ የሚያስገድደን የደካማነት ስሜት ነው። ይህም ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ኃይል ክፍት የሚያደርግ የልብ ዝንባሌ ነው።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ደካማነታችንን ማወቅ፡- ኤር.3፡27፤ 10፡23፤ ዮሐ.15፡5፤ 2ኛ ቆሮ.3፡5።

የጌታ በሁሉም ቦታ መኖር፡- ምሳ.15፡3፤ ኤር.23፡24፤ ኢሳ.66፡1፤ የሐዋ.17፡27።

ጌታ ይሰማናል፡- መዝ.6፡9፤ 35፡4፤ 117፡1፤ 1ኛ ዮሐ.5፡15።

ጌታ ይጠብቀናል፡- ዘፀ.14፡20፤ 2ኛ ነገ.6፡17፤ ዳን.6፡22፤ ዘኪ.2፡5፤ ሉቃ.21፡18።

# ጥናት አሥራ አራት

# ጸሎት የሚደረግባቸው ምክንያቶችና ውጤታቸው

## ዘፍ.18፡16-33

### የጥናቱ ዓላማ

ለምን መጸለይ እንዳለብንና የጸሎታችንን ውጤት መረዳት እንድንችል ነው።

## መግቢያ

ልጆቹ እንዲጸልዩ የጌታችን ፈቃድ ነው። ሕይወታችን በአካባቢያችን ላሉት ሰዎች በረከት መሆን አለበት፣ ይህ ሊሆን የሚችለው ያለማቋረጥ ከእርሱ ኃይል ስንቀበል ነው። ጸሎት በእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ቦታ ያለው ተግባር ነው። ይህም ማለት ጸሎት እግዚአብሔርን ይህንን ስጠኝ ያንን ስጠኝ ብሎ መለመን ብቻ አይደለም። በሕዝቡ ጸሎት የእግዚአብሔር ኃይል ይሠራል።

1. መጸለይ እግዚአብሔርን ማክበር ነው።
   - አብርሃም በሕይወቱ እግዚአብሔርን አከበረ፣ ስለዚህ እግዚአብሔር ለጸሎቱ መልስ ሰጠው፣ ዘፍ.18፡17-19።
   - የልመና ጸሎታችን እግዚአብሔርን ማክበር አለበት፣ ቆላ.3፡17።
   - ጸሎታችን በስግብግብነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ እግዚአብሔር ጸሎታችንን አያከብርም፣ ኢሳ.42፡8።
2. ጸሎት ከእግዚአብሔር የምንፈልገውን ማግኘት ማለት ነው።
   - አብርሃም ስለ ሰዶም ጻድቃን ያለውን ሸክም ለእግዚአብሔር ተናገረ፣ ዘፍ.18፡22።
   - ልመናችንን ለእግዚአብሔር ማስታወቅ እንጂ በምንም ነገር ልንጨነቅ አይገባንም፣ ፊልጵ.4፡6።
   - የዕለት እንጀራችንን እንዲሰጠን ልንጠይቅ ይገባል፣ ማቴ.6፡11።
   - የዕለት መንገዳችንን ሁሉ ለጌታ አደራ እንስጥ፣ መዝ.36፡5።

   ፀሎት እግዚአብሔር በችግራችን ውስጥ እንዲገባ መጋበዝ ማለት ነው።
3. ጸሎት ማለት እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን መቀበል ማለት ነው።
   - አብርሃም በሰዶም ስለነበረው ሎጥና ቤተሰቡ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ተቀበለ፣ ዘፍ.18፡23-32።
   - ብንለምንና ብንፈልግ እግዚአብሔር ለልመናችንና ለፍላጋችን መልስ ለመስጠት ቃል ይገባል፣ ሉቃ.11፡9፣ ዮሐ.14፡14።
   - ጸሎት የእግዚአብሔርን ሰላም ሊሰጠን ይችላል። ፊልጵ.4፡6-7።
   - ለመቀበል መለመን አለብን፣ ዮሐ.16፡24፣ ያዕ.4፡2፣ 5፡13።
4. ጸሎት ማለት እግዚአብሔርን ማወቅ መማር ማለት ነው።
   - ጌታ ከአብርሃም ጋር ተነጋገረ፣ ዘፍ.18፡33።
   - ሕዝቅያስ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ። የጸሎቱም መልስ ለእግዚአብሔር ክብር ነበር፣ 2ኛ ነገ.19፡14-19።
   - ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በኢማሁስ መንገድ ሲሄዱ ከክርስቶስ ጋር ተነጋገሩ፣ ከበፊቱ በበለጠ ሊያውቁትም እንደሚያስፈልጋቸው ተማሩ፣ ሉቃ.24፡15፥ 32። በጸሎት ጊዜያት ጌታን በይበልጥ ለማወቅ ጥማት አለን?
5. ጸሎት ማለት፡-
   - እግዚአብሔርን ማመስገን ማለት ነው፣ ፊልጵ.4፡6፣ ቆላ.3፡15፣ 4፡2፣ 1ኛ ተሰ.5፡18።

እግዚአብሔርን ማወደስ ማለት ነው፥ ዕብ.13፡15፥ ራዕ.4፥11።

6. ጸሎት ስለ ሌሎች ማማለድ ማለት ነው።
   - አብርሃም በሰዶም ስለነበረው ሎጥና ቤተሰቡ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ዘፍ.19፡23-32።
   - ክርስቶስ ለወንጌል ሠራተኞች ጸልዩ ብሏል፤ ማቴ.9፡38።
   - ክርስቶስ ለሚረግሙአችሁ ጸልዩ ብሏል፤ ሉቃ.6፡28።
   - ጳውሎስ «በሥልጣን ከእናንተ በላይ ላሉት ሁሉ ጸልዩ» ብሏል፤ 1ኛ ጢሞ.2፡1-2።
   - ጳውሎስና ያዕቆብ አንዱ ለሌላው መጸለይ እንደሚገባው ገልፀዋል፤ ገላ.6፡2፤ 1ኛ ጢሞ.2፡1፤ ያዕ.5፡16።
   - ጳውሎስ እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ እንዲከፍትለት ጸልዩልኝ ብሏል፤ ቆላ.4፡2-4።

## ጥያቄዎች

1. ጸሎት ምንድን ነው?
2. በሥልጣን ላይ ስላሉት መጸለይ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
3. ስንጸልይ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚታየው ለውጥ ምንድን ነው?
4. ጸሎት እግዚአብሔርን የሚያከብረው እንዴት ነው?
5. እግዚአብሔር ችግራችንን ያውቃል ታዲያ ለምን እንጸልያለን?

## ማጠቃለያ

1. መጸለይ ያለብን ለምንመኘው ሳይሆን ለሚያስፈልገን ነው።
2. ጸሎት የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወታችን እንዲሠራ ያደርጋል፤ መዝ.4፡3፤ 49(50)፡15፤ 85(86)፡5-7፤ ኢሳ.40፡31።
3. ጸሎት እግዚአብሔርን እንድናውቅና እንድናምን ይረዳናል፤ መዝ.18(19)፡14፤ 115(116)፡1-2፤ ኢሳ.26፡3፤ ኤፌ.1፡15-19።
4. የጸሎት መልስ እንደ ጸሎተኛው ኃይል፤ ስሜት ወይም ፍላጎት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ጸሎት እግዚአብሔርን ያከብራል፡- 1ኛ ነገ.18፡37፤ 2ኛ ነገ.19፡19፤ መዝ.49(50)፡23።

መጠየቅ ይገባናል፡- ዮሐ.15፡7፤ ያዕ.1፡5፤ 1ኛ ዮሐ.5፡14።

# ጥናት አሥራ አምስት

# የጸሎት ዕንቅፋቶች መዝ.50(51)

## የጥናቱ ዓላማ

የጸሎታችንን መልስ እንዳናገኝ የሚከለክሉትን ችግሮች አውቀን እንዴት ማስወገድ እንደሚገባን እንድንገነዘብ ነው።

## መግቢያ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እኔ አደርገዋለሁ» ብሏል፤ ዮሐ.14፡14። ታዲያ ብዙውን ጊዜ ከጸለይን በኋላ የማንቀበለው በምን ምክንያት ነው?

ጸሎት ልብን ለጌታ ክፍት ማድረግ መሆኑን ተምረናል። በጸሎት ውስጥ ትግላችን ከጌታ ጋር ሳይሆን ከራሳችን ጋር ነው። ድምፁን እንድንሰማ የእግዚአብሔር መንፈስ ልባችንን ሰላም የሰፈነበት እንዲያደርግልን በጥሞናና በትሑት ልብ መጠበቅ ትግል ነው። ለጸሎታችን መልሶችን መጠበቅ ከመቻላችን በፊት መንፈስ ቅዱስ ሊገልፅልን የሚገባው መሰናክሎች በሕይወታችን ይኖሩ ይሆናል።

1. ንስሐ ያልተገባበት በልብ ውስጥ ያለ ኃጢአት ለጸሎታችን መልስ እንቅፋት ነው።
   - ዳዊት ኃጢአት ሠርቶ ነበር፤ ስለዚህ በመጀመሪያ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ተናዘዘ፤ መዝ.50(51)፡1-2፥ 7፥ 10፥ 14።
   - በመዝ.65(66)፡18 «በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር» የሚል እናነባለን።
2. በልባችን የሚገኝ ጥርጥር ለጸሎት መልስ እንቅፋት ነው።
   - ዳዊት ኃጢአቱ ታላቅ መሆኑን አውቋል፤ ነገር ግን የጌታን ቸርነትና የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ፍርድ በመግፀን በእምነት ቀርቧል፤ መዝ.50(51)፡1-4። ያዕቆብ «በምንም ሳትጠራጠር በእምነት ለምን» ይላል ያዕ.1፡5-8።
   - ኢየሱስ ቅንጣት ያህል እንኳ እምነት ቢኖረን ብዙ እንደሚያደርግልን ተናግሯል፥ ማቴ 17፡20።
3. ተገቢ ያልሆነ ልመና ለጸሎት መልስ እንቅፋት ነው።
   - ዳዊት ሲጸልይ እግዚአብሔር እውነትን እንደሚወድ አውቋል፤ መዝ.50(51)፡6። እግዚአብሔር የተሰበረ መንፈስ፤ የተሰበረና የተዋረደ ልብ እንደሚፈልግ አውቋል፤ መዝ.50(51)፡17።
   - ያዕቆብ በክፉ ስለምንለምን መልስ አናገኝም ብሎ አስጠንቅቋል፤ ያዕ.4፡3። ልመናዎቻችን ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ማክበር አለባቸው። ለልመናችን መነሻ የሚሆኑትን ነገሮች እንመርምር። እግዚአብሔርን ለግል ጥቅማችን ልንጠቀምበት እንሞክራለን? የያዕቆብና ዮሐንስ እናት የጸሎት መነሻ ስሕተት ነበር፤ ማቴ.20፡20-23።
4. በጸሎት አለመትጋት ለጸሎት መልስ እንቅፋት ነው።

- የዳዊት ጸሎት የማያቋርጥ ነበር፤ እግዚአብሔር በችግሩ እንዲገባ ፈቃደኛ እንደነበርም የሕይወት ታሪኩ ያረጋግጣል፤ መዝ.50(51)፤ የዳዊትንም አለመታከት በግልጽ ያሳያል።
- ኢየሱስ ባለመታከቷ የተፈረደላትን ሴት ምሳሌው ተናግሯል፤ ሉቃ.18፡1-8።
- ኢየሱስ በጌቴሴማኒ «እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጉ አልቻላችሁም?» በማለት ደቀ መዛሙርቱን ገስጿቸዋል፤ ማቴ.26፡40።
- እኛ የምቾት ወዳጆች ነን። በዚያን ሌሊት ተግቶ መጸለይ አልተቻላቸውም። ጸሎት ሥራ ሲሆን እኛ ግን ይህንን በትጋት ለመፈፀም ፈቃደኞች አይደለንም። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ሳይሆን ከራሳችን ጋር ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስንጸልይ የእርሱ ኃይል በዚያ አለ። ያዕቆብ «አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም» ይላል፤ ያዕ.4፡2።

## ጥያቄዎች

1. ጸሎት ተግባር ነው፤ ስለዚህ ጸሎት እንዳይደረግ የሚከለክሉ ጥቂት መሰናክሎች ዘርዝሩ።
2. ደቀ መዛሙርቱ በጌቴሴማኒ በጸሎት ሊተጉ ያልቻሉት ለምንድን ነው? በይበልጥ የማንጸልየው ለምንድን ነው?
3. ኃጢአታችን ለጸሎታችን መልስ እንቅፋት ሲሆን የምንወስደው እርምጃ ምንድን ነው?
4. እንደ ማቴ. 20፡20-23 ያሉ ትክክለኛ ያልሆኑ የጸሎት መነሻዎች ሌሎች ምሳሌዎች ስጡ።

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር የጸሎት መሣሪያ ኃይለኛ ነው። የማያልቀውን ኃይሉን ሊጠቀሙበት የሚችሉ ልጆቹ ብቻ መሆናቸውን ገልጿል። እግዚአብሔር ይህንን ኃይል በጥንቃቄ ጠብቆታል። ልጆች እንኳ ፈቃዱንና ዓላማውን በሚቃረን መንገድ ሊጠቀሙበት ቢሞክሩ ያኔውኑ ይቋረጣል።

ለእግዚአብሔር ልናደርግ የምንችለው ከፍተኛው ተግባር ጸሎት ነው።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ተገቢ ያልሆኑ ጸሎቶች፡- ዘኁ.11፡15፤ 1ኛ ነገ.19፡4፤ ዮናስ 4፡3፤ ማቴ.20፡21።

# ጥናት አሥራ ስድስት

# ክርስቶስ በጸሎት ያሳየው ምሳሌነት (ዮሐንስ 17)

### የጥናቱ ዓላማ

ስለ ጸሎት የበለጠ ዕውቀት እንዲኖረን ኢየሱስ የጸለየባቸውን ጊዜያትና በጸሎት የጠየቃቸውን ነገሮች ለማጥናት ነው።

# መግቢያ

ኢየሱስ በዚህ ምድር ሳለ ብዙ ጊዜ ብቻውን በጸሎት አሳልፏል። የማስተማርና የመፈወስ ሥራዎቹ ለዝናው መስራጨት ምክንያት ሆኗል፤ ማር.1፡28። ማለዳ ተነስቶ ጸልዮአል፤ ማር.1፡35። አምስት ሺውን ከመገበ በኋላ ጸልዮአል። አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርቱን ከመምረጡ በፊት ጸልዮአል፤ ሉቃ.6፡12። ጴጥሮስ «ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ» ብሎ የመስከረለትን ምስክርነት ከመቀበሉ በፊት ጸልዮአል፤ ሉቃ.9፡18። ከመሞቱ በፊት በጌቴሴማኒ ጸልዮአል፤ ሉቃ.22፡41-42።

ኢየሱስ ለሥራው ጸሎት ካስፈለገው ለእኛማ የቱን ያህል ያስፈልገን ይሆን? ዮሐንስ 17 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ለእኛም ጭምር የጸለየው ጸሎት ነው። ይህንን ጸሎት በአንድነት እንመልከት፡-

1. ኢየሱስ ለአባቱ ክብር ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡1-5። ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ሊፈጽም ወደዚህ ዓለም መጣ፤ መዝ.40፡8፤ ማቴ.6፡10። ሞቱም አባቱን እንዲያከብር ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡4-5። ስንጸልይ የጸሎታችን መነሻና ምኞታችን ምንድን ነው?
2. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡6-19። ሊለያቸው ስለተቃረበ በስሙ እንዲጠብቃቸው አባቱን ጠይቋል፤ ዮሐ.17፡11። እርሱ ከአባቱ ጋር አንድ እንደሆነ እነርሱም አንድ እንዲሆኑ ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡11። ደስታም እንዲኖራቸው ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡13። በዓለምም ሲልካቸው ከክፉ እንዲጠበቁ ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡15። ለተለየው ወንጌል ለማወጅ ተግባር እንዲቀድሳቸው አባቱን ጠይቋል፤ ዮሐ.17፡18።
3. ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣበትን የማዳኑንም ተግባር እንዲፈጽም ስለራሱ ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡18-19። ኢየሱስ እንዲሁም የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀም እንዲችል ስለራሱ ጸልዮአል።
4. ኢየሱስ ለሚያምኑት፥ ለቤተ ክርስቲያንና አካሉ ለምንሆን ለሁላችን ጸልዮአል፤ ዮሐ.17፡20-26። አንድ እንድንሆን ለአማኞች ሁሉ አንድነት እንደገና ጸልዮአል። ዓላማችን ከሌሎች ምዕመናን ጋር ኅብረታችንንና አንድነታችንን መጠበቅ ነው? የቤተ ክርስቲያን አንድነት አብን እንዲያከብርና ለዓለምም እንዲያስተዋውቀው ጸልዮአል። አንድነታችን ለዓለም ምስክር ነው? ኢየሱስ ፍቅሩ በደቀ መዛሙርቱ እንዲያድር ጸልዮአል፤ እንደጸለየና ቃልም እንደገባ ወዲያው መንፈስ ቅዱስ ወርዷል።

# ጥያቄዎች

1. ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየላቸውን ሦስት ነገሮች ጻፉ።
2. በአማኞች መካከል አንድነት በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?
3. ክርስቶስ ስለ እራሱ የጸለየባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?

# ማጠቃለያ

1. ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የጸለየው በመካከላቸው አንድነትና ፍቅር እንዲኖር ነበር። ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ፍቅር እንጸልያለን?

2. ክርስቶስ አሁንም ለእኛ እየማለደ ነው። እርሱ ታላቁ ሊቀ ካህናችን ነው፤ ዕብ.10፡22-25።

3. ኢየሱስ አንድ ነገር ለመሥራት ከመወሰኑ በፊት፥ ከድል በኋላ፥ «ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ» የሚለውን የጴጥሮስን ምስክርነት ከመቀበሉ በፊትና የአባቱንም ፈቃድ በታማኝነት ለማድረግ ጸልዮአል።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን ሊያከብር መጣ፤ ፊልጵ.2፡9-11።

ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ሊያደርግ መጣ፤ ዮሐ.4፡34፤ 6፡38፤ ዕብ.10፡7።

ኢየሱስ አሁንም እያማለደልን ነው፤ ሮሜ 8፡26-27፤ ዕብ.7፡25።

## ጥናት አሥራ ሰባት

## የጌታ ጸሎት (ማቴ.6፡5-14)

### የጥናቱ ዓላማ

ስለ ጸሎት የተማርናቸውን ነገሮች በመረዳት እንደ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን እንዲያስተምረን እንድንጠይቅ ነው።

### መግቢያ

በጸሎት ትምህርቶቻችን ሁሉ ከተገነዘብናቸው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በሉቃስ 11፡1 እንዳደረጉት «ጌታ ሆይ፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አስተምረን» ለማለት ፈቃደኞች ነን? ጸሎት ሥራ ነው፤ ስለሆነም ወዲያውኑ እንዝላለን፤ ሉቃ.22፡46። ጸሎት ጊዜ ያስፈልገዋል፤ ነገር ግን ራሳችንን በመካድ ለጸሎት ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኞች አይደለንም። ጸሎት የሚስጥር አገልግሎት ነው፤ ነገር ግን ሌሎች ሥራችንን እንዲያዩልን እንፈልጋለን። ጸሎት ምልጃ ነው፤ ውጤትም ማየት እንፈልጋለን። ነገር ግን ለሌሎች ስንማልድ ውጤቱን ወዲያውኑ አናይም ይሆናል። ጸሎት ንጹሕ ልብ ይፈልጋል። ምናልባት ለመተው ፈቃደኛ ያልሆነው ኃጢአት በልባችን ይኖር ይሆናል። ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱና ለእኛ የሰጠን የጸሎት መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

1. ጸሎት በስውር ካለው አባት ጋር የሚደረግ የግል ግንኙነት ነው፤ ማቴ.6፡5-6። ሌሎች እንዲያዩ የሚደረግ ልምምድ አይደለም።

2. ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ መመካት ነው፤ ማቴ.6፡7-8። ብዛት ያላቸው ባዶ ቃላት ብቻ አይደለም። የምንፈልገው ምን እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። ጸሎት ኢየሱስን በችግራችን ማስገባት ማለት ነው።

3. ኢየሱስ ለጸሎት ምሳሌ ሰጥቷል፤ ማቴ.6፡9-13።

   ሀ. የምንቀርበው ወደ ማን እንደሆነ አስቀድመን መገንዘብ አለብን። እንደገና ተወልደን በቤተሰቡ ውስጥ ተቀባይነትን በማግኘታችን እርሱ አባታችን ነው። እግዚአብሔር በየትም ቦታ ቢኖርም እንኳ አማላጃችን ክርስቶስ አሁን በመንግሥተ ሰማይ ነው። ችግራችንን ሁሉ ሊያስወግድ ወደሚችለው ወደ እርሱ በአክብሮት መቅረብ አለብን።

   ለ. ስድስት ልመናዎች አሉ፡-

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ልመናዎች እግዚአብሔርንና ክብሩን የሚመለከቱ ናቸው።

1. «ስምህ ይቀደስ» ይህ የእግዚአብሔርን ቅዱስነት ያረጋግጣል።

2. «መንግሥትህ ትምጣ።» ይህ ልመና እግዚአብሔር በወንዶችና ሴቶች ልብ ውስጥ እንደሚነግሥ ነው።

3. «ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን።» ክርስቶስ «የእኔ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» ብሎ ጸለየ። በጸሎት ወደ እርሱ ስንቀርብ ሐሳባችን ይህ መሆን አለበት። የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ልመናዎች ደግሞ እኛንና ችግሮቻችንን የሚመለከቱ ናቸው።

4. «የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ።» የምንመኘውን ሳይሆን የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን እግዚአብሔር ቃል ይገባል። እንደ አካሎቻችን ነፍሳችንም የዕለት እንጀራና ተሐድሶ ይፈልጋል፤ 1ኛ ጴጥ.2፡2፤ 1ኛ ዮሐ.1፡9።

5. «በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።» በየዕለቱ ለምናደርጋቸው ኃጢአቶች ይቅርታ ያስፈልገናል። ከእግዚአብሔር ጋር ጓደኝነትን ለመፍጠር በየዕለቱ መንጻት አለብን፤ ዮሐ.13፡10። በደላችን ወይም ዕዳችን የገንዘብ ብቻ አይደለም፤ ለበደልናቸውም ባለዕዳዎች ነን፤ ማቴ.5፡39-41።

6. «ወደ ፈተናም አታግባን፤ ከክፉ አድነን እንጂ።» ልንከለክለው ከምንችለው በላይ እንደማንፈተን የሚያስገነዝብ ጸሎት ነው፤ 1ኛ ቆሮ.10፡13፤ 1ኛ ጴጥ.3፡12። ጌታ ድካማችንን ያውቃል፤ ስለዚህም ደግሞ ድካማችንን ስለሚያውቅ እርሱን ለመቃወም የክርስቶስ ኃይል ያስፈልገናል፤ 1ኛ ጴጥ.5፡8-9።

## ጥያቄዎች

1. በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ የመጀመሪያው ሐሳባችን ምን መሆን አለበት?

2. ስንጸልይ ስለ እግዚአብሔር ማስታወስ የሚገባንን ሦስት ነጥቦች ጻፉ።

3. ስለ ራሳችን ማቅረብ ያለብን ምን ዓይነት ጥያቄዎችን ነው?

## ማጠቃለያ

ጸሎታችን የሚያፈራ እንዲሆን በመጀመሪያው መፈለግ ያለብን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ መገንዘብ ነው። ይህም የሚሆነው እርሱን ለማምለክና ለማወደስ ጊዜ በወሰድን ቁጥር ነው።

ቀጥሎም እንደ ፈቃዱ መጸለይ አለብን። ፈቃዱ መሆኑን እርግጠኞች ካልሆንን ፈቃድህ ከሆነ ብለን ለጥያቄያችን መልስን እንዲሰጠን መጸለይ እንችላለን። ከእርሱ ጋር ይበልጥ ጊዜ ስናጠፋ እንዲሁ ፈቃዱን ይበልጥ ማወቅ እንችላለን። ስለ መንፈሳዊና ሥጋዊ የዕለት ችግሮቻችን መጸለይ አለብን።

ስለ ይቅርታ መጸለይና ይቅርታንም በሕይወታችን መለማመድ አለብን። ይህም ስለ ሌሎች የምናደርገውን የምልጃ ጸሎት ይጨምራል።

በመጨረሻም ፈተናን እንድናሸንፍ፤ ብርታትና ጥበብ እንድናገኝ መጸለይ አለብን። የእኛ ድርሻ ፈቃደኛ መሆን ብቻ ነው። ኃይሉን እርሱ ይሰጣል።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ክብር ለእግዚአብሔር ስም፡- መዝ.29፡2፤ 34፡3፤ 57፡5፤ ኢሳ.25፡1፤ ሚል.1፡11፤ ራዕይ 5፡13።

ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፡- መዝ.40፡8፤ 143፡10፤ ማቴ.26፡42፤ ያዕ.4፡15።

ጸሎት ስለ ችግር፡- ፊልጵ.4፡19፤ ያዕ.2፡15-16።

ጸሎት ስለ ይቅርታ፡- 2ኛ ቆሮ.7፡14፤ መዝ.86፡5፤ ሉቃ.11፡4፤ ማቴ.18፡21፥ 35፤ ማር.11፡26፤ ሉቃ.23፡34፤ 2ኛ ቆሮ.2፡7፤ ኤፌ.4፡32፤ ቆላ.2፡13፤ 1ኛ ዮሐ.2፡12።

ጸሎት ስለ ፈተና፡- ምሳ.1፡10፤ ሉቃ.10፡19፤ 22፡31-32፤ ሮሜ 6፡13፤ 1ኛቆሮ.10፡13፤ ኤፌ.6፡13፤ ዕብ.2፡18፤ ያዕ.4፡7፤ 2ኛ ጢሞ.3፡17።

## ጥናት አሥራ ስምንት

# በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ታላላቅ ጸሎቶች

### የጥናቱ ዓላማ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሠፈሩት ጸሎቶች አማካይነት ስለ ጸሎት በይበልጥ ከተማርን በኋላ አጥጋቢ ውጤት የሚያስገኝ ጸሎት መጸለይ እንድንችል ነው።

## መግቢያ

1ኛ ቆሮ.10፡6፥ 11 የእሥራኤላውያን ታሪክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተመዘገበው ለእኛ ምሳሌ እንዲሆነን ነው ይላል። ከልምዳቸውና ከሕይወታቸው መማር አለብን። ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ጸሎቶችም መማር እንችላለን። ጸሎቶቻቸው ለምን አጥጋቢ እንደነበሩ እንመልከት።

1. ሙሴ በጸሎት ታላቅ አማላጅ ነበር። በዘፀ.32፡11-14ና ዘኁ.14፡13-20 ያለውን አንብቡ። ሙሴ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የገባውን ቃል ኪዳን በድፍረትና በመተማመን ጠቅሷል፤ በአለመታዘዛቸው ጊዜም እንኳ እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው ጸልዮአል፥መዝ. 105(106) ስለ ሙሴ እንዲህ ይላል፡- ባያማልድና ቁጣውንም ከእነርሱ እንዲያርቅ ባያደርግ ኖሮ እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ያጠፋቸው ነበር። ሙሴ የዋህ በጸሎት ግን ደፋር ነበር፤ ዘኁ.12፡3። እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ያለውን ቃል ኪዳን እንዲያስብ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮአል። በእርግጥ ለሌሎች ማማለድን ተምረናል?
2. በእምነቱ ምክንያት በኤልያስ ልመና ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል ነበረበት፤ ያዕ.5፡17-18 እና 1ኛ ነገ.18፡36-39ን አንብቡ። ኤልያስ በእሥራኤል የበአልን አምልኮ ተቃወመ። በእሥራኤል አገር ለሦስት ዓመት ዝናብ ባልዘነበበት ወቅት የእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ ጋር ነበር። እንደገናም ከበዓል ነቢያት ጋር በነበረው ክርክር መስዋዕቱን ለማቃጠል በጸሎቱ አማካይነት የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወደቀች። ኤልያስ እንደገና ጸልዮአል፤ በዚህም የሦስት ዓመቱ ድርቅ ማብቂያ

እንዲሆን እንደገና ዘንቧል። ለክብሩ በእምነት መጠየቅን ብንማር የእግዚአብሔር ኃይል ለልጆቹ ሁሉ ቅርብ ነው።

3. የዳንኤል ጸሎት የንስሐና የልመና ጸሎት ነበር። ዳንኤል ምዕ.9ን አንብቡ። ዳንኤል እግዚአብሔር ሕዝቡን ከስደት አውጥቶ ወደራሳቸው ምድር እንደሚመልሳቸው የሚያሳየውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በኤር.25፡11 አንብቡ። ነገር ግን ዳንኤል የተማረኩበት ከኃጢአታቸው የተነሳ መሆኑን ስላወቀ የእሥራኤልን ኃጢአት ተናዞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቋል። ዳዊት «በልቤስ በደልን አይቼ ከሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር» እንዳለ እንዲሁ ደግሞ ዳንኤልም ይህንን አውቋል፤ መዝ.66፡18። የክፉ ኃይላት የጸሎትን ኃይል ስለሚያውቁ የዳንኤልን የጸሎት መልስ አዘግይተዋል፥ ዳን.10፡12። ሆኖም እግዚአብሔር ለጸሎቱ መልስ በመስጠት የክፉት ኃይሎችን አሸንፏል። ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ እንደሚጣል ባወቀ ጊዜም እንኳ በጸሎት ትጉ ነበር፥ ዳንኤል 6፡10። እግዚአብሔርም ከማንኛውም ዓይነት ጉዳት ሰውሮታል፥ ዳን.6፡22። ዓለም በጸሎት ውስጥ ያለውን ይህንን ዓይነቱን ኃይል ሊረዳው ሊያሸንፈውም አይችልም።

4. ሰለሞን በጥበብ መግዛት እንዲችል ጸልዮአል፤ 1ኛ ነገ.3፡5-9። የጸለየው ለራሱ ክብር ሳይሆን ሕዝቡን በጥበብ ማስተዳደር እንዲችል ነበር። እግዚአብሔር በእንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት ይደሰታል።

5. ሐና ወንድ ልጅ መውለድ እንድትችል ጸለየች፤ 1 ሳሙ.1፡9-18። ሐና ለጸሎቷ መልስ እንደምታገኝ በእግዚአብሔር ተማመነች። ልጇንም አገልጋዩ እንዲሆን ለእግዚአብሔር ልትሰጠው ቃል ገባች። ለልጆቻችን ያለን ምኞት ምንድን ነው?

6. ነህምያ ንጉሡን ለማነጋገር ጥበብ ስለፈለገ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ነህ.2፡4። የነህምያ ጸሎት አጭር ሳይሆን አይቀርም፤ ነገር ግን ውጤቱ ያማረ ነበረ።

7. ሕዝቅያስ ኢየሩሳሌም በተከበበች ጊዜ ጸለየ፤ 2ኛ ነገ.19፡14-19። ሕዝቅያስ ከመልእክተኞቹ የማስፈራሪያውን ደብዳቤ ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። ስሙ በአሕዛብ ሁሉ ፊት ለማስከበር እንዲያድናቸው እግዚአብሔርን ጠየቀ። የጸሎታችን መነሻ ምንድን ነው? መዝ.62፡5-8ና ያዕ.4፡3ን አንብቡ።

8. ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩት ክርስቲያኖች ጸልዮአል፤ ኤፌ.3፡14-21። የጳውሎስ ፍላጎት የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ዕድገት ነበር፤ ቆላ.1፡9-27ን አንብቡ።

9. በዮሐንስ 17 ያለውን የክርስቶስን ጸሎት እንደገና ከልሱ።

## ጥያቄዎች

1. ያጠናናቸውን ጸሎቶች ውጤት ጥሩ ያደረጓቸው ጥቂት ባሕርያት ምንድን ናቸው?
2. እነዚህን ጸሎቶች በጸለዩባቸው ጊዜያት የሙሴ፥ ኤልያስና ዳንኤል ሁኔታ እንዴት ነበር? በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ የእያንዳንዳቸው ሁኔታ እንዴት እንደነበር ግለጹ። እነዚህን ዛሬ እናንተ ለምትገኙባቸው ሁኔታዎችም ተጠቀሙባቸው።

## ማጠቃለያ

የእነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች ጸሎቶች ውጤቶች ጥሩ ያደረጓቸው ነገሮች፡-

1. እግዚአብሔር መልስ በተሰጣቸው ጸሎቶች እንዲከበር መመኘታቸው፥
2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዲፈፀም መለመናቸው፥
3. ጥበብን ለራሳቸው ክብር ሳይሆን ለሥራ ወይም ላጋጠማቸው ችግር መጠየቃቸው፥
4. የራሳቸውንና የሕዝባቸውን ኃጢአት መናዘዛቸው፥
5. እውነት ያልሆነውን ትምህርት በመቃወማቸውና
6. በሕይወታቸው ታዛዦችና እግዚአብሔርንም አክባሪዎች መሆናቸው ነበር።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

የቅዱሳን ጸሎቶች፡-

የአብርሃም - ዘፍ.18፡23-33፥

የኢያሱ - ኢያ.7፡4-8፥

የጌዴዮን - መሳ.6፡2፥ 11-16፥ 22-24፥ 25-40፤ 7፡1-22፥

የያቤድ - 1ኛ ዜና 4፡9-10፥

የሳሙኤል - 1ኛ ሳሙ.12፡19-23፤ 15፡10-11፥ 35፥

የዳዊት - መዝ.51፥

የኢዮሳፍጥ - 2ኛ ዜና 19፡1-3፤ 20፡3-15፥

የዕንባቆም - ዕን.1፡2፤ 2፡1-4፤ 3፡17-19፥

የኤርምያስ - ኤር.1፡4-10፥ 17፥ 19።

# መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጨረሻ ነገሮች
# የሚያስተምረው ትምህርት
## ጥናት አሥራ ዘጠኝ
## ሞት (ሉቃ.16፡19-31)

**የጥናቱ ዓላማ**

**ሞት በመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምን እንደሆነ እንድንረዳ ነው።**

## መግቢያ

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሰው ልጅ «በውኑ ሰው ከሞተ ተመልሶ ሕያው ይሆናል?» እያለ ሲጠይቅ ኖሮአል፤ ኢዮብ 14፡4። ኢየሱስ «በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሥኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ» በማለት ራሱ መልሱን ሰጥቷል፤ ዮሐ.5፡28-29። ስለ ሞትና ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት የእግዚአብሔር ቃል ምን ይነግረናል?

1. ሞት ምንድን ነው?

   እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም ሞት ማለት መለየት ማለት ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ የሰው ከዚህ ዓለም መለየት ማለት ነው። የሕይወት ማብቂያ ማለት አይደለም።

ሀ. ሞት በብሉይ ኪዳን አመለካከት፡-

1. ሞት ጨለማማና ጥላማ ቦታ፤ ዝምታ ያለበት፤ መግባባት የሌለበት፥ አንዳች ማስተዋል የሌለበት ቦታ ተደርጎ ተቆጥሮ ነበር፤ ኢዮ.10፡21፤ ምሳ21፡16፤ ኢሳ26፡14፤ መዝ.6፡5፤ መዝ.87(88)፡10-12። በሕያዋን ሞት የሚታወሰው በድንጋጤና ተስፋ በመቁረጥ ነው፤ መዝ. 38(39)፡13፤ 1ኛ ሳሙ.28፡17-19።
2. ሲኦል የሞቱ ሰዎች ማረፊያ ቦታ ነው፤ ሉቃ. 16፡19-31። በብሉይ ኪዳን ሰዎች ከሞቱበት ጊዜ እስከ ትንሣዔ ወቅት ድረስ የሚቆዩበት ሥፍራ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። ጻድቃን ከኃጢአን ተለይተዋል። በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ናቸው፥ መዝ.138(139)፡8። አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በሲኦል የነበሩ ነፍሳት ነፍሳቸውን የሳቱና የማያውቁ እንዳልነበሩ ተገንዝበዋል፤ 1ኛ ሳሙ.28፡11-15፤ ኢሳ.14፡9።

ለ. ሞት በአዲስ ኪዳን አመለካከት፡-

1. ክርስቶስ ከሞቱና ትንሣኤው በፊት ስለ ባለጠጋው ሰውዬና አልአዛር ምሳሌ ወይም ማብራሪያ ሰጥቷል፤ ሉቃ.16፡19-31። ከትምህርቱ ባሕርይ የተነሣ ይህ ከምሳሌ በላይ ሳይሆን አይቀርም። «የአብርሃም እቅፍ»

በሲኦል የበጎዎች ወይም የጻድቃን ቦታ ነበር። «የስቃይ ቦታ» በሲኦል ለክፉዎች የተዘጋጀ ቦታ ነበር። ከአንዱ ወደ ሌላው ማለፍ አይችሉም ነበር።

2. ከመስቀል ሞቱ በኋላ ክርስቶስ እራሱ ወደ ሲኦል ወርዶ በቁጥጥር ሥር ላሉት ነፍሳት ሰብኳል፤ 1ኛ ጴጥ.3፥19። በሰይጣንና ሞት ላይ የተቀዳጀውንም ድል አውጇል፤ ንስሐ ገብተው እንዲያምኑ አልጠራቸውም። ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሣ እንጂ በዚያ አልቆየም፤ 1ኛ ቆሮ.5፥20።

ሐ. ዛሬ የሚሞቱ አማኞች በሲኦል አይደሉም። አንድ አማኝ እንደሞተ ወዲያውኑ ከክርስቶስና ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚሆን አዲስ ኪዳን ያስተምራል፤ ሉቃ. 23፥43፤ 2ኛ ቆሮ.5፥6-8፤ ፊልጵ. 1፥23፤ ራዕ.6፥9፤ 7፥9፤ 15፥2። ክርስቶስ እስከሚመለስ ድረስ የሙታን ትንሣኤ አይሆንም፤ 1 ተሰ.4፥16። ሰው ከሞተ በኋላ አካል አልባ እንዳልሆነ ያስተምራል፤ 2ኛ ቆሮ.ምዕ.5።

2. ሁለተኛው ሞት ምንድን ነው?

ኢየሱስና ጳውሎስ እንደገና ያልተወለዱ በመንፈስ ሙት መሆናቸውን ያስተምራሉ። በመንፈስ ሙት ማለት አሁን በሥጋ ሕይወታችን እያለን እንኳ ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው፤ 1ኛ ዮሐ.5፥12። በሉቃስ 16 ባለጠጋው ሰውዬ በሕይወቱ የተትረፈረፈው የተመቻቸለት ሲሆን በመንፈስ ግን ሙት ነበር፤ ሉቃ.16፥19።

ሀ. የመጀመሪያው ሞት የሥጋ ሞት ነው። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ከሚነጠቁት ሰዎች በስተቀር ሰው ሁሉ ይሞታል።

ለ. ሁለተኛው ሞት የሚፈፀመው ገና ወደፊት ነው። ባለጠጋው ሰውዬ በዚያ መካከለኛ ቦታ በሲኦል ነበር። በሁለተኛው ሞት ውስጥ አልነበረም። ሁለተኛው ሞት በመጨረሻው ጊዜ ያላመኑትና ሰይጣን የመጨረሻ ፍርድ የሚቀበሉበት የእሳት ባሕር ነው፤ ራዕ.2፥11፤ 20፥6፥ 14-15። ሁለተኛው ሞት በክርስቲያኖች ላይ ኃይል የለውም። አስቀድመን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል፤ ዮሐ.5፥24። ሞት ለክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማይ መግቢያ በር ብቻ ነው፤ ምክንያቱም የሞትን ኃይል ክርስቶስ ድል ነስቶታል፤ 1ኛ ቆሮ.15፥54-57። ክርስቲያኖች በመሆናችን እንጽናናለን፤ ተስፋ እንደሌላቸው አናዝንም፤ 1ኛ ተሰ.4፥13።

3. ስለ ሙታን ሦስት አስተያየቶች፡-

ሀ. ከሥጋ ሞት በኋላ ነፍስ ሕያው ነች። ይህ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ነው። ጌታችን ራሱ በሥጋ ሞተ፤ «በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤» 1ኛ ጴጥ. 3፥19። ክርስቶስ ሊሞት ሲያጣጥር የነበረውን ወንበዴ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» አለው። ባለጠጋው ሰውና አልአዛር ራሳቸውን አልሳቱም ነበር፤ ሉቃ. 16፥22-23። ጳውሎስ ቢሞት ከጌታ ጋር እንደሚሆን ያውቅ ነበር፤ ፊልጵ.1፥22-24።

ለ. አንዳንድ ሰዎች ነፍስ ከሥጋ ጋር ትሞታለች፤ ትንሣኤንም ትጠባበቃለች ይላሉ። ይህንን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም።

ሐ. ሌሎች ደግሞ ነፍስ በማንቀላፋት ኑሮዋን ትቀጥላለች ይላሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በቂ የሆነ ማረጋገጫ የለም፤ 1ኛ ቆሮ.11፥30ና 15፥6 የሥጋ ሞት ማለታቸው ነው። በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሞት አብዛኛውን ጊዜ «እንቅልፍ» ተብሎ

ይጠራል፤ 2ኛ ሳሙ.7፡12፤ 1ኛ ነገ.2፡10፤ 11፡43፤ 22፡50፤ ኢዮ.14፡12፤ መዝ.13፡3፤ ዳን.12፡2፤ ማቴ.5፡39፤ 9፡24፤ ዮሐ.11፡11፤ የሐዋ.7፡60፤ 13፡36፤ 1ኛ ቆሮ.15፡51፤ 1ኛ ተሰ.4፡13።

## ጥያቄዎች

1. የብሉይ ኪዳን የሞት ፍርሃት የተወገደው እንዴት ነበር?
2. ክርስቶስ ሞቶ ከመነሳቱ በፊት ሲኦል ምን እንደነበር ግለጹ።
3. በአዲስ ኪዳን አመለካከት የአማኞች ሞት ምንድን ነው?
4. የሞቱት ትንሣኤ የሚሆነው መቼ ነው?
5. ሁለተኛው ሞት ምንድን ነው?
6. ሁለተኛውን ሞት አማኞች የማይፈሩት ለምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

አብርሃም ባለጠጋውን ሰው «ልጄ ሆይ፤ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ፤» አልአዛርንም እንዴት እንዳስተናገድከው አስብ አለው። ይህ ዓይነት ሐዘን ከሥቃያቸው አንዱ ክፍል ሳይሆን አይቀርም። ንስሐ እንዲገቡ ዕድል ሳላቸው እምቢተኛ መሆናቸውን ያስታውሳሉ።

ክርስቲያኖች አሁን በታማኝነት ቢኖሩ ሲሞቱ ምንም ጸጸት ወይም ፍርሃት አይኖርባቸውም።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

መንፈሳዊ ሞት፡- ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ.2፡1፤ ዮሐ.5፡12።

ሞት የኃጢአት ውጤት ነው፤ ዘፍ.2፡17።

ሰው ከአፈር ተፈጠረ፤ ወደ አፈርም ይመለሳል፡- መዝ.16፡10፤ የሐዋ.2፡27፤ 13፡35።

እስጢፋኖስ ጌታ ወዳለበት ሥፍራ ቀረበ፡- የሐዋ.7፡59።

ስለ ልጁ ሞት የዳዊት አመለካከት፡- 2ኛ ሳሙ. 12፡23።

## ጥናት ሃያ

## ትንሣኤ (1ኛ ቆሮ.15)

### የጥናቱ ዓላማ

ትንሣኤ ለክርስትና እምነታችን ምን ያህል ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን እንድንረዳ ነው።

## መግቢያ

በአማኞች ላይ ከፍተኛ ጉጉት የሚያሳድር የክርስትና እምነት ባሕርይ የትንሣኤ ተስፋ ነው። ትንሣኤ የክርስትናን ኃይማኖት ከሌሎች ኃይማኖቶች ሁሉ የተለየ ያደርገዋል። ሐዋርያት የወንጌል መልእክት ኃይል የሆነውን የክርስቶስን ትንሣኤ ተረድተው ነበር።

1. አረማውያንና አይሁዶች ስለ ትንሣኤ ያላቸው አስተሳሰብ፡-

ግብፃውያንና ባቢሎናውያን በአረማዊ እምነታቸው ስለ ትንሣኤ መጠነኛ የሆነ አስተሳሰብ ነበራቸው፤ ነገር ግን ይህ እነርሱ የሚያስቡት ትንሣኤ የተስፋ ትንሣኤ አልነበረም። ግሪኮች በተለይም ፕላቶ ተብሎ ይጠራ የነበረው ፈላስፋ አካል ለእውነተኛ ሕይወት መሰናክል ነው ብለው በማሰብ ነፃ ለመሆን ይፈልጉ ነበር። ነፍስ በሕያውነት እንደምትኖር ሲያምኑ በአካል ትንሣኤ ግን አያምኑም ነበር። ስለ ሙታንም ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ በአቴና በጳውሎስ ላይ አፌዙበት፤ የሐዋ. 7፡32። ከአይሁድ አብዛኛዎቹ አካል እንደሚነሳ ነገር ግን በፊት የነበረው ፍጥረታዊ አካል እንደሚሆን ያስቡ ነበር። ሰዱቃውያን ግን በትንሣኤ ሙታን አያምኑም ነበር፤ ማቴ.22፡23። ክርስቶስ መሳሳታቸውን አረጋግጦላቸዋል፤ ማቴ.22፡23-33። በዙሪያቸው የነበሩ የነዚህ ሰዎች ሐሳቦች በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮችን ፈጥሯል።

2. ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን፡-

ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ተጠቅሶ ቢገኝም ይህን ያህል ጉልህ አይደለም። በዳን.12፡2 እጅግ በጣም ግልጽ የሆነ ዐረፍተ ነገር ተሰጥቶአል። «በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ደግሞ ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና።» ኢዮ.16፡26ንና ኢሳ26፡16ን ተመልከቱ።

የትንሣኤ ትምህርት መሠረት የክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤ ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ስለዚህ ትንሣኤ ምንም አያውቁም። በብሉይ ኪዳን ከሞት የተነሡትና በወንጌሎች ውስጥ ክርስቶስ ከሞት ያስነሳቸው ሰዎች ወደ ዱሮው ፍጥረታዊ አካላቸውና ሕይወታቸው ተለውጠው ነበር። ይህ እውነተኛው ትንሣኤ አልነበረም።

3. ትንሣኤ፤ 1ኛ ቆሮ.15፡1-58

ሀ. የክርስቶስ ትንሣኤ፤ 1ኛ ቆሮ.15፡1-11። ጳውሎስ የወንጌልን ፍሬ ሐሳቦች ይሰጣል፤ ወንጌል በትንሣኤ ላይ እንዴት እንደተመሠረተም ያሳያል።

ክርስቶስ፡- 1. ለኃጢአታችን ሞተ፤

2. ለሦስት ቀናት በመቃብር ውስጥ ቆየ፤ በእርግጥ የሞተ መሆኑን ያረጋግጣል።

3. እንደገናም በሦስተኛው ቀን ተነሣ። በትንሣኤ አካሉም ሳለ ከአምስት መቶ የሚበልጡ ምስክሮች አዩት።

ለ. የክርስቲያኖች ትንሣኤ፤ 1ኛ ቆሮ.15፡12-19።

በቆሮንቶስ የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ነፍስ ከሥጋ ተለይታ በሌላ ዓለም ወዳለ ጨለማማ መኖሪያ ትገባለች የሚለውን የግሪኮችን ሐሳብ እስካሁን የሙጥኝ ብለው ነበር። ጳውሎስ ይህንን ማመን የክርስቶስን ትንሣኤ መካድና የእምነታቸውንም መሠረት ማበላሸት መሆኑን ተናግሯል።

ክርስቶስ ተነሥቶአል፤ የአዲሱ ትንሣኤ አካልም በኩር ነው በማለት ጳውሎስ አውጇል። የክርስቶስ ትንሣኤ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንደሚነሱ ተስፋ ነው፤ 1ኛ ተሰ4፡13-18። የአዳም ኃጢአት ለሰው ዘር ሁሉ ሞትን አስከተለ፤ ክርስቶስ ግን ሕይወትና ተስፋ ሰጠ። የክርስቶስ ትንሣኤ የመጀመሪያ ሆኗል፤ የአማኞች ሁሉ ትንሣኤም በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጊዜ ይሆናል። በዚያን ጊዜም የዘመን ፍጻሜ

ይሆናል። ክርስቶስ አሁን ዓለምን በመቆጣጠር ላይ ነው፡ ሲመለስ ግን ተፎካካሪ ኃይላትን ሁሉ የእግሩ መረገጫ ያደርጋቸዋል፤ መዝ. 109፡1። ይህ በአዲስ ኪዳን ብዙውን ጊዜ የሚጠቀስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ነው። ክርስቶስ በትንሣኤው ሞትን ድል አድርጓል፤ 2ኛ ጢሞ.1፡10።

ምንም እንኳ ሞት አሁንም በዓለም ውስጥ ቢኖርም ክርስቶስ ሲመለስ ይወድማል፤ ራዕ.20፡14። ጳውሎስ ትንሣኤ ባይኖር ኖሮ የወንጌል መልእክትና ወንጌሉንም በመስበክ የሚደርስበት ስቃይ ሁሉ በከንቱ ይሆን እንደነበር ተናግሯል። ጳውሎስ የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች የትንሣኤውን ተስፋና ደስታ ያሰጣቸውን የአረማዊያንን ሐሳብ ተጽእኖ ተገንዝቧል። እንዲነቁና ስለ እግዚአብሔርም ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው ገስጿቸዋል።

4. የትንሣኤ አካል፤ 1ኛ ቆሮ.15፡35-58።

የትንሣኤ አካል አይሁዳውያን እንዳሰቡት የፍጥረታዊ አካል መታደስ አልነበረም። እንደ ስንዴ ፍሬ በመጀመሪያ ካልሞተ ሕያው የሚሆን ነገር የለም፤ ዮሐ.12፡24።

አዲሱ የትንሣኤ አካል አሮጌውን አካል ይመስላል፤ ይህኛው ግን አዲስ፥ ክቡርና የማይጠፋ አካል ነው። ለሚቀጥለው ሕይወት አስፈላጊና ተስማሚ የሆነ አዲስ ዓይነት አካል እግዚአብሔር ይሰጠናል። በክርስቶስ መመለስ ጊዜ በክርስቶስ የሞቱት ሁሉ የማይጠፋውን አዲሱን አካላቸውን ወዲያውኑ ይቀበላሉ።

ሞት ፈጽሞ ድል ይነሳል! ክርስቲያኖችን በክርስቶስ እምነታቸው እና አገልግሎታቸው ታማኝና ጽኑ አድርጎ የሚያቆያቸው ተስፋ ይህ ነው።

## ጥያቄዎች

1. የአረማዊያንና ያልዳኑ አይሁዳውያን ሐሳብ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ላይ የነበረው ተጽእኖ ምን ነበር?
2. ሦስቱ የወንጌል መልእክት መሠረተ ሐሳቦች ምንና ምን ናቸው?
3. ትንሣኤ የክርስትና እምነት መሠረት የሆነው ለምንድን ነው?
4. ክርስቶስ ከሞት ለመነሣቱ ምን ማረጋገጫ አለን?
5. የትንሣኤ ተስፋ በክርስቲያኖች ውስጥ ማሳደር ያለበት ጽኑ ፍላጎት ምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

1. ኢየሱስ ከአርባ ቀናት በላይ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ሰዎች ታይቶአል፤ ለትንሣኤው ሌላ ምን ምስክር ያስፈልጋል?
2. ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል በዛ ያሉ በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች የክርስቶስን ትንሣኤ ታሪካዊ ሐቅ ሊያስተባብሉ ሞክረዋል፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ ወንጌል ከሚጥልብን ተጠያቂነት ነፃ ነን የማለት አሳብ ስላላቸው ነው። የክርስቶስ ከሞት መነሣት የክርስትና እምነት መሠረት ነው።
3. የክርስቶስ ትንሣኤ ዋና ማስረጃ በተለወጠ ሰው ሕይወት ውስጥ የክርስቶስ ኃይል መገለጥ ነው።
4. የትንሣኤ ውጤቶች:-

ሀ. የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል፤ 1ኛ ቆሮ.15፡7።

ሌ. የጌታ ኢየሱስ አምላክነት ማረጋገጫ ነው፤ ሮሜ 1፡4።

ሐ. መቀደስ ያስችለናል፤ ሮሜ 4፡25፤ 8፡34፤ የሐዋ.13፡39።

መ. ለአማኞች ሁሉ ተስፋ ይሰጣል፤ 1ኛ ቆሮ.15፡20።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን፡- መዝ.16፡10፤ ኢዮ.19፡25-27፤ ኢሳ.26፡19።

የክርስቶስን ትንሣኤ ይመሰክራሉ፡- ማቴ.28፡6፤ ዮሐ.20፡14-18፤ ማቴ.28፡8-10፤ ሉቃ.24፡34፤ ዮሐ.20፡24-29።

የክርስቲያኖች ትንሣኤ፡- 1ኛ ተሰ.4፡13-18።

የአላመኑት ትንሣኤ፡- ራዕ.20፡4-6።

# ጥናት ሃያ አንድ

# የክርስቶስ ዳግም ምፅአት (1 ተሰ.4፡13-5፡11)

### የጥናቱ ዓላማ

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ያለንን ዋስትና ለማረጋገጥና ስለዚህም ያለንን እውቀት ደግሞ ለማሳደግ ነው።

## መግቢያ

ኢየሱስ «እንደገና እመጣለሁ» በማለት ተስፋ ሰጥቷል። ጌታን የሚወዱ ሁሉ በዚህ ተስፋ ያምናሉ። በመጀመሪያ እግዚአብሔርን በሥጋ ለመግለጽ መጣ። በታላቅ ክብርና ኃይል እንደገና ዳግም ይመጣል።

1. በእግዚአብሔር ድል አድራጊነት ሁሉ ነገር እንደሚያበቃ ብሉይ ኪዳን ይጠቁማል። ኢሳ24-27ን አንብቡ። ብሉይ ኪዳን ሰማያዊ ኃይላት ቢሆኑ ምድራዊ፤ የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ ውድቀት፥ የሞትንም ድል መመታት እንደሚገልፁ ያሳያል፤ ኢሳ24፡21፤ 27፡1።
   ከጥቂቶቹ ተስፋዎች መካከል አንዱ ለሆነው ስለ አካላዊ ትንሣዔ ይናገራል፤ ኢሳ26፡19።
   ዳን. ምዕ. 12ን አንብቡ። ትንቢተ ዳንኤል የእግዚአብሔር ሰዎች ምንም እንኳ በአሕዛብ መንግሥት ሥር በባርነት ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል በመሆኑ ድል እንደሚያደርግ ያስተምራል። የወደፊቱን በጥልቅ በመመርመር ዘላለማዊውን ተስፋ ያሳያል፤ ዳን.12፡2-10።
2. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የአዲስ ኪዳን ተስፋ፤ 1ኛ ተሰ.4፡13-18።
   በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ አንዳንዶች ስለ ቅዱሳን ሞት ስላልገባቸው ጳውሎስ ጽፎላቸዋል። በክርስቶስ የሞቱት ክርስቶስ ሲመለስ እንደሚነሱ አረጋግጦላቸዋል። ሕያው ሆነው ከቀሩት ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል በደመና ይነጠቃሉ፤ የሐዋ.1፡11።
3. የክርስቶስ መምጫ መቃረቡን የሚያሳዩ ምልክቶች፤ 1ኛ ተሰ.5፡1-11። የክርስቶስ ዳግም ምፅአት እርግጠኛ ነው፤ መቼ እንደሆነ ግን አይታወቅም፤ 1ኛ ተሰ.5፡1። የእግዚአብሔር ሰዎች የታሪክ አቅጣጫ የሚለወጥበት ጊዜ መቃረቡን ማየት

እንዲችሉ ቃሉ በቂ መረጃ ይሰጣል። እግዚአብሔር እቅዱን በሚመለከት አላዋቂ ወይም ደንቆሮ እንድንሆን አይፈልግም፤ ዘፍ. 18፡17፤ አሞ. 3፡7፤ ዳን. 12፡9-10። ክርስቶስ ፈሪሳውያን የዘመኑን ምልክት መለየት ባለመቻላቸው ገስጿቸዋል፤ ማቴ.16፡2፥ 3። ጳውሎስ «ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም» ብሏል፤ 1ኛ ተሰ.5፡4-5። ጴጥሮስ ስለ ትንቢት ሲናገር በጨለማ ሥፍራ የሚበራ መብራት ነው» ብሏል፤ 2ኛ ጴጥ.1፡19።

4. የምልክቶቹ ዓላማ፡-

ሀ. ዘመኑን የመለክቱናል፤

ለ. የሚፈጸም መሆኑንም ያረጋግጡልናል።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ምልክቶች ክርስቶስ ዛሬ ይመጣል ማለት ሳይሆን ቃሉ እውነት መሆኑን ያመለክታሉ። «ቀኑ መቅረቡን ስናይ» ቃሉ እንደምልክት ሆኖ የሚገልጽልን ምንድን ነው? ዕብ. 10፡25።

ሀ. የኢየሩሳሌም ጥፋት - ሉቃ.21፡20፥ 24፤

ለ. የአይሁድ ከተበተኑበት ወደ አገራቸው መመለስ - ዘዳ.30፡3፤

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠረው ታላቅ ክሕደት - 1ኛ ጢሞ.4፡1፤ 2ኛ ጢሞ.3፡1-8፤

መ. በክርስቲያኖች መካከል ግዴለሽነትና የፍቅር መቀዝቀዝ - ራዕ.3፡10፤ ማቴ.24፡12፤

ሠ. ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ነቢያት ያሥታሉ - 1ኛ ጢሞ.4፡1-3፤ ማቴ.24፡5፥ 11፥ 24፤

ረ. ረሃብ፤ ጦርነትና ቸነፈር ይበዛል - ማቴ. 24፡6-7፤ ራዕ.6፡2-4፤

ሰ. ወንጌል በዓለም ዙሪያ ሁሉ ይሰበካል - ማቴ.24፡14፤

ሸ. መጥፎ ዘመን ይመጣል - 2ኛ ጢሞ.3፡1-5፥ 13፤

ቀ. የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ትምህርት ተቃውሞ ይደርስበታል - 2ኛ ጴጥ.3፡3-4፤

በ. ክርስቲያኖች ይሰደዳሉ - ማቴ.24፡9፤

ተ. የክርስቶስ ተቃዋሚ ይከሰታል፤ 2ኛ ተሰ.2፡1-12።

5. የክርስቶስ መመለስ፡-

ክርስቶስ በሥጋ ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፤ 1ኛ ተሰ.4፡16፤ የሐዋ. 1፡11፤ ራዕ.1፡7፤ ማቴ.24፡30።

በድንገት ይመጣል፤ 1ኛ ተሰ.4፡16፤ 1ኛ ቆሮ.15፡23፥ 51-52፤ 2ኛ ጴጥ.3፡10፤ ማቴ.25፡13።

በክብርና ድል አድራጊነት ይመጣል፤ 1ኛ ተሰ.4፡16፤ 2ኛ ተሰ.1፡7-10፤ ራዕ.19፡11-16።

6. ክርስቶስ ሲመለስ የሚሠራው ሥራ፡-

ሀ. የራሱ የሆኑትን ሊቀበልና ደኅንነታችንንም ሊፈጽም ይመጣል፤ 1ኛ ተሰ. 4፡16-17፤ 5፡8-9፤ 1ኛ ዮሐ.3፡2፤

ለ. በአማኞች ሥራ ፍርድ ይሰጣል፤ ሽልማትም ይሰጣል፤ ሮሜ 14፡10፥ 12፤ 1ኛ ቆሮ.3፡13-15፤ 2ኛ ቆሮ.5፡10፤

ሐ. በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል፤ ማቴ. 25፡32-46፤

መ. በሰይጣንና ባላመኑት ሁሉ ላይ ይፈርዳል፤ ራዕ.20፡11-15፤

ሠ. ሞትን ያጠፋል፤ 1ኛ ቆሮ.15፡24-26፤

ረ. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ይፈጥራል፤ ራዕ.21፡1-7።

7. የክርስቶስ መመለሻ ጊዜ፡-

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የክርስቶስ ምፅአት መቼ እንደሚሆን የሚያቀርቡት ሐሳብ የተለያየ ነው። ስለ ጌታችን ዳግም ምፅአት ሦስት አስተያየቶች አሉ። ሁሉም እግዚአብሔር ለአይሁድ በተለይም ለአብርሃም ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ግንኙነት አላቸው። እነዚህን ሦስት አስተያየቶች በትምህርት 21 ውስጥ እናጠናቸዋለን።

# ጥያቄዎች

1. በተሰሎንቄ ክርስቲያኖች መካከል ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የነበረው አለመግባባት ምን ነበር?
2. የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ስለሚቀድሙት ምልክቶች ተወያዩ። ዛሬ ለእናንተ በግልጽ የሚታዩአችሁ የትኞቹ ናቸው?
3. የክርስቶስን ዳግም ምፅአት አብራሩ። ክርስቶስ የሚመለሰው መቼ ነው?
4. ክርስቶስ ሲመለስ ምን ያደርጋል?

# ማጠቃለያ

ወደፊት አንድ ቀን ክርስቶስ ራሱ በሥጋ ይመጣል። ይህ ሐቅ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በይበልጥ ግልጽ ቢሆንም እንኳ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም ዳግም የተረጋገጠ ነበር። እግዚአብሔር ዓለምን ከመመሥረቱ በፊት የነበረው እቅድ እየተከሰተ ነው። የእርሱ የሆንን ሁሉ ይህንን አንድ ቀን እንረዳዋለን። ዋናው ነገር ለምፅአቱ በትጋት እያገለገልን መጠባበቅ ነው።

# ተጨማሪ መግለጫዎች

የሐሰት ትምህርት፡- ማቴ.24፡10፤ ሉቃ.18፡8፤ 2ኛ ተሰ.2፡3።

ሐሰተኛ ነቢያት፡- 2ኛ ጴጥ.2፡1-2፤ የሐዋ.20፡29-30።

ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል፡- መዝ.67፡2፤ ራዕ.5-9።

የክርስቲያኖች መሰደድ፡- ማቴ.10፡17-18።

የክርስቶስ ተቃዋሚ፡- ራዕ.13፡1-8፤ ራዕ.19፡20፤ 20፡10።

የክርስቶስ መመለስ፡- ቲቶ 2፡13፤ ማር.13፡26፥ 35-36፤ ሉቃ.21፡27፤ የሐዋ.1፡9-11።

# ጥናት ሃያ ሁለት

## የወደፊቱ ሁኔታዎች (ዘፍ.17፡ 1-22)

### የጥናቱ ዓላማ

ምንም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ወደፊት በሚሆኑት ነገሮች ቅደም ተከተል ላይ ባይስማሙም ግልጽና መሠረታዊ ሐቅ በሆነው የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ላይ ይስማማሉ። ይህ አለመስማማት ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ምክንያት መሆን እንደሌለበት መረዳት እንድንችል ነው።

## መግቢያ

ሰዎች ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ለማወቅ በመናፈቅ ይኖራሉ። ሆኖም ቀኑን መወሰን አደገኛ ጉዳይ ነው። ብሉይ ኪዳን ፍፃሜ የማያገኝ ትንቢት የሚናገር ነቢይ በድንጋይ መወገር አለበት ብሎ አዟል፤ ዘዳ13፡1-8፥ 8፥ 20-22።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ብዙ ትንቢቶች በመፈፀማቸው ትክክለኛ መሆናቸውን ማየት እንችላለን። ሆኖም ገና ወደፊት የሚፈፀሙ ጥቂት ነገሮች አሉ። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ወደፊት ስለሚፈፀሙት ነገሮች ቅደም ተከተል የተለያየ ሐሳብ አላቸው።

በሚከተሉት ግን ሁሉም ይስማማሉ፡-

1. ክርስቶስ ይመለሳል፤ የሐዋ.1፡11።
2. የሚመለስበትን ቀንና ሰዓት አናውቅም፥ ማቴ.24፡44።
3. ተግተን መጠበቅ፤ መጸለይና መዘጋጀትም አለብን፥ ማቴ.24፡44።

ስለ ወደፊቱ ሁኔታ ያሉት የተለያዩ ሐሳቦች እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በመጀመሪያ ቃል ኪዳኑን እንመልከት።

1. ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን በዘፍ.17፡1-22 ተገልጿል።

ሀ. ከአብርሃም ጋር የተደረጉ ተስፋዎቹ አብዛኞዎቹ በቀጥታ ተፈፅመዋል። ለምሳሌ ምድር፥ አገልጋዮች፥ እንስሳት፥ ብርና ወርቅ ተሰጥተውታል፤ ዘፍ.13፡14-15፥ 17፤ 15፡7፤ 24፡34-35።

የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆኗል፤ ተደስቷል፤ ዘፍ.18፡17፤ ያዕ.2፡23።

አብርሃም ከሞተ በኋላ ዘሩን የሚባርኩ ይባረካሉ፤ የሚረግሙ ግን ይረገማሉ፤ ዘፍ. 14፡12-20፤ 20፡2-18፤ ዘዳ 30፡7፤ ኢሳ14፡1-2፤ ማቴ.25፡40።

የምድር ቤተሰዎች ሁሉ የአብርሃም ዘር በሆነው በክርስቶስ ይባረካሉ፤ ገላ.3፡16።

ለ. ለአብርሃም ተሰጥተው ገና ካልተፈፀሙት ተስፋዎች መካከል አንዱ እርሱም ለእርሱና ለዘሩ ቃል የተገባለትን ምድር አለመውረሱ ነው፤ ዘፍ.15፡8 አንብቡ።

እግዚአብሔር በተከፈለው መስዋዕት መካከል በመመላለስ የተጠቀመበት መንገድ እንደሚያመለክተው እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ፍጹም ነበር፤ ዘፍ.15፡9-17።

ቃል ኪዳኑ ለአብርሃም ልጅ ለይስሐቅና ለልጁ ያላንዳች ገደብ እንደገና ተረጋግጦዋል፤ እንደዚሁም እግዚአብሔር የዳዊት ዘር፥ ዙፋንና መንግሥት ለዘላለም እንደሚመሠረት ቃል ኪዳን ገብቷል። ያም ዘር ክርስቶስ ነው፤ ሉቃ.1፡32-33።

እግዚአብሔር ትዕዛዜን ባይጠብቁ እቀጣቸዋለሁ እንጂ ቃል ኪዳኔ አይፈርስም ወይም አይለወጥም ብሏል፤ መዝ.89፡30-37፤ ኢሳ.9፡6-7፤ ኤር.23፡5-8፤ ሆሴ.3፡4-5፤ አሞ.9፡11-12፤ ዘካ.14፡4-9፤ 14፡4-11።

ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ስለ ገባው ቃል ኪዳን የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች፡-

ቃል ኪዳኑን የሚፈፅመው ክርስቶስ መሆኑን ሁሉም ይስማማሉ። መቼ እንደሚፈፅመው ግን የሚያቀርቡት ሐሳብ ይለያያል።

1. ክርስቶስ አሁን በሰማይ ሆኖ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦአል?

2. መንግሥቱ ቤተ ክርስቲያን ናት?

3. ክርስቶስ በምድራዊ መንግሥት የሚገዛበት ወቅት ገና ወደፊት ነው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች ስለ ወደፊቱ ለተሰጡት የተለያዩ አስተያየቶች መሠረት ናቸው። ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች የተሰጡት ሦስት መሠረታዊ ሐሳቦች ለአብርሃም የተሰጠው ቃል ኪዳን ገደብ አለው ወይስ የለውም የሚለው ሐሳብ ለዳዊት መንግሥት የተሰጠው ተስፋ ተፈፅሞአል ወይስ አልተፈፀመም በሚለው ላይ የተመሠረተ ነው።

2. ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች የተሰጡ ሦስት አስተያየቶች፡-

ሀ. ጥቂቶች የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ከክርስቶስ የአንድ ሺህ ዓመታት ግዛት በኋላ ይሆናል ብለው ያምናሉ። ይህንን ለሚያምኑት በቤተ ክርስቲያን ሥራ መልካም ዘመን ይመጣል፤ ለአብርሃምና ለዳዊት የተሰጡት ቃል ኪዳኖች መፈጸም ለእሥራኤል ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ይሆናል ብለው ያምናሉ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ይህ አስተያየት ተቀባይነቱ እየቀነሰ ነው። የክርስቶስ መንግሥት በምድር ላይ ይሆናል። ይህም የአይሁድ መንግሥት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መንግሥት ነው። በሰዎች ልብ ሆኖ ይገዛል እንጂ ንጉሡ ክርስቶስ በምድር ላይ አይኖርም፤ ከሺህ ዓመታት በኋላ ይመለሳል። በዚያን ጊዜም የሞቱት ሁሉ አጠቃላይ ትንሣኤና የሰዎች ሁሉ አጠቃላይ ፍርድ ይሆናል፤ ዘላለማዊ ሕይወትም ይጀምራል።

ክርስቶስ የሚመጣው ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ነው ብለው የሚያምኑት፥ ያልተፈፀሙት ለአብርሃም የተሰጡት ቃል ኪዳኖች ቃል በቃል ሳይሆኑ በቤተ ክርስቲያን ይፈፀማሉ ብለው ያስተምራሉ።

በአንጺህ ዓመታት
ግዛት እስከሚጀምር
ድረስ ጽድቅ እየተጨመረ
ይሄዳል።




ሊ. ጥቂቶች ወደፊት የአንድ ሺህ ዓመታት ግዛት አይኖርም ብለው ያምናሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ነው። አሁን እግዚአብሔር ምድርን እየገዛ ነው። ክርስቶስ እስኪመለስ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ዘመን የተሰኘው እስኪፈፀም ድረስ በዘመናችን ያሉት ሁኔታዎች ይበልጥ መጥፎ እየሆኑ ይሄዳሉ። ከክርስቶስ ዳግም ምፅአት በኋላአያኔውኑ አጠቃላይ ትንሣኤና ፍርድ ይሆናሉ።

የክርስቶስ የአንድ ሺህ ዓመታት ግዛት ያሁኑንም ዘመን ያጠቃልላል ብለው የሚያስተምሩት ለአብርሃም ስለተሰጡት ቃል ኪዳኖች መፈፀም ያላቸው አስተያየት የሚከተሉት ናቸው:-

1. አንዳንዶች ቃል ኪዳኖች በሰለሞን ዘመን ተፈፅመው ነበር ብለው ያምናሉ፤ 1ኛ ነገ. 4:21። ሆኖም እሥራኤል ምድሩን ሁሉ አልወረሰም፤ ለዘላለምም አላገኘውም።
2. አንዳንዶች ቃል ኪዳኑ በመታዘዛቸው ላይ የተመሠረተ ነበር። እሥራኤል ባለመታዘዙ ሁኔታዎቹ ሊሟሉ አልቻሉም ይላሉ።
3. ሌሎች ምናልባትም አብዛኞዎቹ፣ ቤተ ክርስቲያን ቃል በቃል ሳይሆን ቃል ኪዳኑን በተለየ መንገድ ታሟላለች ብለው ያምናሉ። ለእሥራኤል ለተሰጡት ተስፋዎች መንፈሳዊ ትርጉም በመስጠት በቤተ ክርስቲያን ተፈጽመዋል ይላሉ።

አሁን ክርስቶስ
በሰማይ እየነገሠ
ነው።




የሐሰት ትምህርት

እነዚህ ምሁራን ራዕይ ምዕ.20ን ሲያብራሩ በመጀመሪያውና በሁለተኛው የክርስቶስ ምፅአት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ በሰማይ ያሉትን ነፍሳት ይገልፃል ብለው ያስተምራሉ።

ሐ. አንዳንዶች የክርስቶስ ዳግም ምፅአት ከአንድ ሺህ ዓመት መንግሥት በፊት ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ክርስቶስ መንግሥቱን ይመሠርታል ብለው ያምናሉ። ክርስቶስ በእርግጥ እንደ ንጉሥ በምድር ላይ ይነግሣል። በአንድ ሺህ ዓመቱ መንግሥት ጊዜ አይሁዳውያን ለአብርሃምና ለዳዊት የተሰጡትን ተስፋዎች ይለማመዳሉ። ባለንበት ዘመን ክፋት እየበዛ ስለሚሄድ ከክርስቶስ ዳግም ምፅአት በፊት የሚሆነውን የታላቅ መከራ ዘመን ያስከትላል። ክርስቶስ ሲመለስ ለአንድ ሺህ ዓመታት የሚቆይ መንግሥት ያቋቁማል። ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ያልዳኑት ከሞት ተነስተው ይፈረድባቸዋል። ይህ ትርጉም ለአብርሃምና ለዳዊት እንዲሁም ለልጆቻቸው የተሰጡትን ተስፋዎች ቃል በቃል የሚያብራራ ነው። አዲስ ኪዳን አይሁድን ከቤተ ክርስቲያን መለየቱን ይቀጥላል፤ ለዚህም ለአይሁድ የተሰጠው ተስፋ በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን በአይሁድ በኩል ይፈጸማል፤ 1ኛ ቆሮ.10:32፤ ሮሜ 11:26።

## ጥያቄዎች

1. ስለ ወደፊቱ አማኞች ሁሉ የሚስማሙባቸው ሦስት መሠረታዊ ሐቆች ምንና ምን ናቸው?
2. የተለያዩ ምሁራን የወደፊት ሁኔታዎችን ቅደም ተከተል አስመልክተው ሲያስተምሩ ለአብርሃምና ለዳዊት ከተሰጡት ቃል ኪዳኖች መካከል በየትኛው ነጥብ ላይ አይስማሙም?
3. በ1.(ለ) መጨረሻ ላይ ያሉትን ጥቅሶች አንብቡ። ለአይሁድ የተገባው ቃል ኪዳን በመታዘዝ ላይ የተመሠረተ ነው ወይስ አይደለም?
4. ለአይሁድ የተሰጡት ተስፋዎች የሚፈጸሙት በአይሁድ በኩል እንጂ በቤተ ክርስቲያን በኩል አይደለም ብሎ የሚያምነው የትኛው አመለካከት ነው?
5. ለአብርሃም ከተሰጡት ተስፋዎች መካከል ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸመው የትኛው ነው?

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ይመጣል፤ እስከሚመጣ ድረስም የምንሠራው ሥራ አለን ብለው ሁሉም ከተስማሙ በኋላ ወደፊት በሚሆኑት ነገሮች አተረጓጎም ላይ ግትር ብሎ መከራከሩ ጥቅም አለው? ይልቁንስ ሥራውን እንቀጥል፤ ሉቃስ 19:13።

ከመጀመሪያው የክርስቶስ ምፅአት በፊት ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የተለያዩ አተረጓጎሞች ነበሩ። የመጀመሪያ ምፅዓቱን በትክክል የተረጎመ አንድ ቡድን እንኳ የለም።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

አይሁድ ከቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው:- የሐዋ.1:6፣ ሮሜ 11:25-26፣ ሉቃስ 21:24።

ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ተስፋዎች:- 1ኛ ተሰ.5:9፣ 1:9-10፣ ሉቃስ 21:36፣ ራዕ.3:10።

ዳግም ምፅአቱን በትጋት ጠብቁ:- ሮሜ 8:19-25፣ 1ኛ ቆሮ.1:7፣ ቲቶ 2:13፣ ያዕ.5:8-9።

# ጥናት ሃያ ሦስት

# የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት

ዮሐ.14:1-3 1ተሰ.4:13-18 1ቆሮ.15:51-57

### የጥናቱ ዓላማ

ውጤቱ ተስፋና ንፁህ ሕይወት የሆነውን የክርስቶስን የመመለስ ሐቅ በልባችን ውስጥ በሕያውነት እንድናስቀምጠው ነው።

## መግቢያ

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ ሲያነጋግር በዘመናት ታሪኳ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ተስፋ የሆነውን ቃል ኪዳን ሰጥቶአቸዋል። ያም ቃል ኪዳን ኢየሱስን እንደገና የማየትና ከእርሱም ጋር የመሆን ተስፋ ነው፤ ዮሐ.14:1-3። በተፈጥሮአችን ተለውጠን እርሱን እንመስላለን የሚለውንም ተስፋ ይጨምራል፤ 1ዮሐ.3:1-3። ክርስቲያኖች ሁሉ የእነዚህን ቃል ኪዳኖች መፈጸም በናፍቆት ይጠባበቃሉ። ሆኖም ወደፊት መቼ እንደሚፈፀሙ በሚያቀርቡት ሐሳብ ሁሉም አይስማሙም።

1. ኢየሱስ:-

ሀ. ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ፤ ዮሐ.14:3።

ለ. ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ዮሐ.14:3።

ሐ. ወደ እኔ እወስዳችኋለሁና ዮሐ.14:3።

መ. እኔን ትመስላላችሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶልናል፤ 1ዮሐ.3:1-3።

2. ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ሲል የሚመጣው መቼ ነው?

ሀ. አንዳንዶች ከታላቁ የመከራ ዘመን በኋላ ይመጣል ብለው ያምናሉ። እነዚህ ቤተ ክርስቲያን በመከራና ችግር ዘመን እንደማታልፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ማረጋገጫ አያቀርቡም። ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቁጣ ትተርፋለች እንጂ ከታላቅ መከራ ዘመን ግን አትተርፍም ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ከመጨረሻዎቹ ነገሮች አንፃር መጽሐፉን ቃል በቃል አይተረጉሙም። የታላቁ መከራ ዘመን ለሰባት ዓመታት ብቻ እንደሚሆን እርግጠኞች አይደሉም። ስለ ታላቁ መከራ

ዘመን የሚያወሱት ምንባቦች ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሆን ለይተው አያመለክቱም።

ከታላቅ መከራ በኋላ ይመጣል ብለው የሚያምኑት ታላቁ የመከራ ዘመን የጌታ ምፅአት መቃረብ ምልክት ነው ይላሉ።

በታላቁ መከራ የሚኖሩት «ምርጦች» ቤተ ክርስቲያን ናቸው ብለው ያምናሉ። በእሥራኤልና በቤተ ክርስቲያን መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት አያደርጉም።

ክርስቶስ ሊነግሥ በሚመጣበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ጌታን ለመገናኘት ትነጠቃለች፤ ነገር ግን ክርስቶስ ወዲያውኑ ግዛቱን ይመሠርታል ብለው ያምናሉ።

ለ. አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ መከራ በፊት ከዓለም ትወሰዳለች ብለው ያምናሉ። ይህ አመለካከት ቤተ ክርስቲያን በተጠንቀቅ ስሜት እንድትጠባበቅ ያሳስባል። በመጀመሪያው መቶ ዓመት በቤተ ክርስቲያን የነበረውን የማንጸት ተስፋ ይሰጣል። እነዚህ ከሌሎቹ ይልቅ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ሕያው አድርገው ጠብቀውታል። ከታላቁ መከራና ችግር በፊት ይመጣል ብለው የሚያምኑት ታላቁን የመከራ ዘመን ኃይለኛ በመሆኑ ክርስቲያኖችም ሁልጊዜ ከሚሰቃዩበት ስደት የተለየ አድርገው ያዩታል።

ታላቁ የመከራ ዘመን ሁለት ዓላማዎች አሉት:-

1. «የአሕዛብ ዘመናት» የተሰኘውን ይደመድማል፤
2. ለክርስቶስ የአንድ ሺህ ዓመታት መንግሥትና ለእሥራኤል እድሳትና መሰብሰብ ያዘጋጃል። ለሰባቱ ዓመታት የመከራ ዘመን ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ቤተ ክርስቲያን ትነጠቃለች። ከዚህም በኋላ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በኋላ ትመለሳለች።

ሐ. አንዳንዶች ክርስቶስ ከታላቁ መከራ ዘመን መካከል ይመጣል ብለው ያምናሉ።

መ. አንዳንዶች መልካም ያደረጉት ብቻ ከታላቁ መከራ ዘመን በፊት ከዓለም ይወሰዳሉ ብለው ያምናሉ።

3. ክርስቶስ ዳግም ምፅአቱን ለምን ያዘገያል?

ክርስቶስ በመጀመሪያ ሲመጣ ሁሉ ለመምጣቱ ዝግጁ ሆነው ሳሉ መጣ፤ ገላ.4፡4። ዳግም የሚመጣበት ትክክለኛ ጊዜ አለ። ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ማንም እንዲጠፋ ፈቃዱ አይደለም፤ ጴጥ.3፡9። እግዚአብሔር ሰው ጊዜን እንደሚለካ አይለካም፤ 2ጴጥ.3፡8።

4. ክርስቲያኖች ዳግም ምፅአቱን መጠባበቅ አለባቸው፤ ማቴ.25፡13፤1 ተሰ.5፡5፤ ራዕ.3፡11። የምንሠራው ሥራ አለን፤ ስለዚህ ትጉ መሆን አለብን። ዝግጁ ሆነን እንድንገኝ ከኃጢአት መጠበቅ አለብን።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቲያኖች ሁሉ የሚስማሙባቸው ተስፋዎች ምን ምን ናቸው?
2. ስለ ቤተ ክርስቲያን ንጥቀት የተሰጡት አራት አስተያየቶች ምንና ምን ናቸው?
3. የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ስሜት ሕያው አድርጎ ያቆየው የትኛው አስተያየት ነው?

## ማጠቃለያ

ለዳግም ምፅአቱ ሁልጊዜ ዝግጁ እንዲሆኑ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በጥብቅ አሳስቧል። የክርስቶስ ዳግም ምፅአት በኖህ ዘመን እንደሆነው ጎርፍ በድንገት ስለሚሆን እርሱ እስከሚመለስ ድረስ የጌታ አገልጋዮች በትጋት ማገልገል አለባቸው። ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ያለው የትርጉምና የመረዳት ልዩነት በእግዚአብሔር መካከል ላለው ኅብረት መፍረስ ምክንያት መሆን የለበትም። ስለጌታ መመለስ መሠረታዊውን ሐቅ የሚቀበሉ ሁሉ እንደ እውነተኛ አማኞች መቆጠር አለባቸው።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ነቅቶ መጠበቅ:- ማር.13፡33፤ ማቴ.26፡41፤ 1ቆሮ.10፡12፤ 16፡13፤ 1ጴጥ.5፡8፤ ቲቶ 2፡13፤ ያዕ.5፡8-9፤ ይሁዳ 21።

የአካል መዳን:- ሮሜ8፡19-25።

## ጥናት ሃያ አራት

## ፍርድ (ማቴ.25)

### የጥናቱ ዓላማ

ጻድቅ አምላክ በኃጢአት ላይ መፍረድ ያለበት መሆኑን ለመገንዘብና በመንግሥታትና በግለሰቦች ላይ የሚፈርደውን ፍርድ ትክክለኛነት ለማየት ነው።

## መግቢያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ፍርድ ስናነብ የአለፈው፥ የአሁን እና የወደፊት ፍርዶች የተጣመሩ ናቸው። በዓለም መጨረሻ የሚሆን አንድ ታላቅ አጠቃላይ ፍርድ የለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ፍርዶች በጊዜ፤ በቦታ፤ ፍርድ በሚሰጥባቸው ጉዳዮችና ውጤታቸው የተለያዩ ናቸው። ማቴ.25 ከእነዚህ ፍርዶች ሦስቱን ይገልፃል።

1. የስም ክርስቲያኖች ፍርድ:- ማቴ.25፡1-13።

በቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን እንደሚያውቁት የሚናገሩ ነገር ግን የሕይወቱ ባለቤት ያይደሉ አሉ። አምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅት በአማኞች ማኅበር ውስጥ ያሉ ብዙውን ጊዜም የሚመስሉአቸው ነገር ግን ገና እውነተኛ አማኞች ያልሆኑ ናቸው። በዚህ ምሳሌ ሙሽራው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስን የሚከተሉት ድንግሎች የተባሉት ናቸው፤ ራዕ.14፡4።

አንዳንዶች ተስፋቸውን የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆናቸው ወይም ከክርስቲያኖች ጋር ባላቸው ማኅበር ላይ ይጥላሉ። የክርስትና ሕይወትን ያስተጋባሉ፤ ነገር ግን ክርስቶስንና አዲስ ሕይወቱን አይቀበሉም፤ ኢሳ55፡6፤ 2 ቆሮ.6፡2። ሙሽራው ምፅአቱን አዘገየ። አሥሩ ቆነጃጅት ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። ብዙ ክርስቲያኖችም እንኳ ቸልተኛና ግዴለሽ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም ጌታ ምፅአቱን እያዘገየ ነው ብለው ያምናሉ፤ ነገር ግን አሁንም የክርስቶስ ናቸው። አምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅት ወደ ሠርጉ ለመግባት ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ብለው ቢጮሁ ሙሽራው «አላውቃችሁም» አላቸው፤ ማቴ.7፡21። በፍርድ ቀን ጊዜ ክርስቶስ የሚሰጠውን ሕይወት ተቀብለው ያልተዘጋጁ ብዙዎች ይኖራሉ፤ 2 ቆሮ.6፡2፤ ምሳ.27፡1።

2. ለአልዳኑት ፍርድ ይኖራል።

ይህ ፍርድ ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ይባላል፤ እርሱም የመጨረሻው ፍርድ ነው፤ ራዕ.20፡11-15። ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈው በእሳት ባሕር ውስጥ ይጣላሉ። እንደ አምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅቶች ጌታ «አላወቅኋችሁም» ይላቸዋል።

3. ዩአማኞች ፍርድ ይኖራል፤ ማቴ.25፡14-30፤ ሮሜ 14፡10።

የአማኞች ኃጢአት አስቀድሞ በክርስቶስ መስቀል ላይ ተፈርዶበታል። የአማኞች ፍርድ እንደ ሥራቸው ሽልማት ለመቀበል የሚያስችላቸው በሥራቸው ላይ የሚሰጥ ፍርድ ነው። እግዚአብሔር ለሁሉ ሰው ዕድልና ችሎታን ይሰጣል። ብንጠቀምባቸው ሌሎች ዕድሎችንና ችሎታዎችን ይጨምርልናል፤ ማቴ.25፡15። እግዚአብሔር በሌለን ሳይሆን ባለን መጠን ይፈርዳል፤ 2 ቆሮ.8፡11-12፤ ሉቃስ 12፡47-48። አንዳንዶች ከሌሎች የበለጠ ዕድልና ችሎታ አላቸው። እግዚአብሔር አንድ ሰው ባለው ችሎታ መጠን ይፈርድበታል። በጥቃቅን ነገሮች መታመን ለታላቅ ዕድል ያበቃል፤ ማቴ.25፡21-23። አንዳንዶች ምክንያትም ይፈጥራሉ። እግዚአብሔር የሚሰጠውን ዕድልና ችሎታ ስለማይጠቀሙበት እግዚአብሔር ያላቸውንም ይነጥቃቸዋል፤ ማቴ.25፡24-25፥ 28-29፤ ማር.4፡25። አማኞች ያላቸው ችሎታ ተፈጥሮአዊ ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር ሊያገለግሉት ከሚያስችላቸው ዕድልና ኃይል ጋር ስጦታዎችን ለልጆቹ ሰጥቷል። በታማኝነት እንጠቀምባቸዋለን? 2 ቆሮ.3፡9-17።

ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር ለደኅንነት የሰጠውን ዕድል እንቢ ላሉና ችሎታቸውን ወይም ሊጠቀሙበትና ሊያከማቹት የተፈቀደላቸውን ሀብት በትክክል የማይጠቀሙ ከሐዲዎችንም የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ያልዳኑትም ደግሞ እንደ ሥራቸው ፍርድን ይቀበላሉ፤ ራዕ.21፡12-13፤ ማቴ.11፡24።

እግዚአብሔር አሕዛብን የሚፈርድባቸው የራሱን ሕዝብ ማለት አይሁዶችን ካደረጉላቸው አቀባበል አንፃር ይሆናል፤ ማቴ.25፡31-46፤ ኢዩ.3፡2። በፍጹም ጻድቅ ሕዝብ ስለሌለ በግለሰቦች ላይ የሚሰጥ ፍርድ ይኖራል፤ የመቀበላቸው መሠረት የጻድቃን መልካም ተግባር ሳይሆን የእግዚአብሔር ፀጋ በሕይወታቸው መረጋገጥ ነው። ጻድቃን ያልሆኑት በተግባራቸው መልካም የሆነ ወይም በጥረታቸው ጽድቅ የሚያገኙ ይመስላቸዋል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር «አላውቃችሁም» ይላቸዋል። ይህ ፍርድ በታላቁ መከራ ዘመን የሚኖሩ አሕዛብ ፍርድ ሳይሆን አይቀርም፤ ኢዩ.3፡2። አሕዛብ የሚፈረድባቸው አይሁዶች በታላቁ መከራ ዘመን ሲሰደዱ ባደረጉላቸው አቀባበል መጠን ይሆናል። ይህ በእርግጥ ክርስቲያኖችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ለዘላለም ሕይወት የሚያበቃን መልካም ተግባራችን አይደለም፤ ነገር ግን ለእርሱ ታዛዥ በመሆን ለምንሠራው ሥራ ሽልማት እናገኛለን። ሰዎች ሥጋዊ ጥማት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ጥማትም አላቸው፤ ማቴ.25፡35።

5. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሌሎች ፍርዶች፡-

ሀ. የመስቀሉ ፍርድ ተፈጽሟል።

በመስቀሉ ላይ ሰይጣን ተፈርዶበታል፤ በአማኞች ላይ የነበረውም ኃይል ተደምስሷል፤ 1ኛዮሐ.3፡8፤ ዕብ.2፡14። በመስቀሉ ላይ የአማኝ ኃጢአት ተፈርዶበታል፤ ተወግዷልም፤ ቆላ.2፡13-14፤ ዮሐ.5፡24፤ 2 ቆሮ.5፡21፤ ገላ.3፡13፤ 1 ጴጥ.2፡24።

ለ. በአማኞች ሕይወት በአሁኑ ዘመን የሚሰጥ ፍርድ፡-

ኃጢአት በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ በገባ መጠን የማያቋርጥ የኃጢአት ፍርድ መኖር አለበት፤ 1 ዮሐ.1፡5-9፤ 1 ቆሮ.11፡29-32። ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ኃጢአት ላይ በየዕለቱ በሚገባ የማይፈርዱ ከሆነ መንፈሳዊ ዕድገታቸውን ይከለክላል፤ ለምስክርነታቸው እንቅፋት ይሆናል፤ እግዚአብሔርንም ማዋረድ ነው። አሁን በዚህ ሕይወት ከእግዚአብሔር ቅጣትን ሊያስከትል ይችላል፤ 1ኛ ቆሮ.5፡5፤ 11፡30፤ 1 ጢሞ.1፡20፤ 1 ሳሙ.7፡14፤ 12፡13-14።

ሐ. የእሥራኤል ፍርድ፡-

ይህ ምናልባት ከታላቁ የመከራ ዘመን በኋላ ሳይሆን አይቀርም፤ ሕዝ.20፡33-44።

መ. ኃጢአት ያደረጉ መላእክት ፍርድ ይሰጣል፤ ይሁዳ 6፤ 2 ጴጥ.2፡4፤ 1ኛቆሮ.6፡3። በመጀመሪያ መልአክ የነበረው ሰይጣን ይፈረድበታል፤ ራዕ.20፡10።

## ጥያቄዎች

1. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ ሁለተኛው የሞት ፍርድ የሚፈረድባቸው ለምንድን ነው?
2. እግዚአብሔር በአማኞች ላይ የሚፈርደው እንዴት ነው?
3. እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት ለክርስቲያኖች የሚሰጠውን ችሎታ፥ ስጦታና ዕድል የማይጠቀሙበት ከሆነ ውጤቱ ምን ይሆናል?
4. የመልካም ሥራዎች ዓላማ ምንድን ነው?
5. በመስቀል ላይ የተፈረደባቸው ማንና ምን ነበሩ?
6. ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ የሚሰጠው መቼና ለማን ነው?
7. ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ባለው ኃጢአት ላይ በየዕለቱ መፍረድ ያለባቸው ለምንድን ነው?

## ማጠቃለያ

1. ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ ተመድቦባቸዋል፤ ዕብ.9፡27።
2. እግዚአብሔር በሐቅ ይፈርዳል፤ ሮሜ 2፡2፤ ራዕ.19፡2፤ ዘኁ. 32፡23።
3. እግዚአብሔር ልዩነት አያደርግም፤ ሮሜ 2፡6። አያዳላም፤ ሮሜ 2፡11።
4. እግዚአብሔር በውስጥ ሁኔታና በውጫዊ ፀባይ ላይ ይፈርዳል፤ ሮሜ 2፡16።

## ተጨማሪ መግለጫዎች

የአማኞች ፍርድ፡- ዕብ.1፡13፤ ሮሜ 8፡1፤ 2 ዮሐ.8፤ ማቴ.16፡27፤ ሉቃስ 14፡14።

የማያምኑ ሰዎች ፍርድ፡- 2 ቆሮ.5፡11፤ 1 ቆሮ.11፡31።

ስለ መልካም ሥራ፡- ገላ.2፡16፤ ሮሜ 9፡32፤ 11፡6፤ 2ኛጢሞ.1፡9፤ ቲቶ 3፡5-6።

# ጥናት ሃያ አምስት

## የዘመን መጨረሻ (ራዕ.20-22)

**የጥናቱ ዓላማ**

ስለ ዘመን መጨረሻ የተሰጡትን ቃል ኪዳኖችና ማስጠንቀቂያዎች ለማጥናት ነው።

## መግቢያ

«ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው» ራዕ.1፡3።

«ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ እንደባለአዕምሮ አስቡ፤ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ» 1 ጴጥ.4፡7።

«እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ማቴ.28፡20። እነዚህን ተግሣጾችና ቃል ኪዳኖች በማሰላሰል ላይ ሆነን የዮሐንስ ራዕይ የወደፊቱን የዘላለም ሕይወት በዓይነ ሕሊና እንድንቃኘው ይረዳናል። እንደ ኢሳ. 24-27፤ ዳን. ምዕ. 12 እና ሌሎችም በትንቢተ ዳንኤል ያሉ ምንባቦች እግዚአብሔር በመጨረሻ ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርግ ያመለክታሉ።

1. የክፉዎች መድረሻ

ሀ. ሰይጣን፡-

ሰይጣን በአንድ ሺህ ዓመት የክርስቶስ መንግሥት ወቅት ይታሠራል፤ ራዕ.20፡1-6። ለጥቂት ጊዜ ተፈትቶ አሕዛብን ለማሳሳት ይወጣል፤ ኢየሩሳሌምንም የሚከቡ በቁጥራቸው የበረከቱ አመፀኞች ይሰበሰባል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በነገሩ ውስጥ ገብቶ ከሰማይ በወረደ እሳት ያወድማቸዋል፤ ራዕ.20፡7-9። ሰይጣን ከአውሬውና ከሐሰተኛው ነቢይ ጋር ወደ እሳት ባሕር ተጥሎ ለዘላለም ይሰቃያል፤ ራዕ.19፡20፤ 20፡10።

ለ. ያልዳኑት፡-

ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ ሁሉ ይነሳሉ። በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊትም ቆመው እንደ ሥራቸው ፍርድን ይቀበላሉ። ይህ የቅጣት ደረጃ መኖሩን ያስገነዝባል፤ ራዕ.20፡11-15።

2. አዲስ ፍጥረት፡-

ሀ. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም ይታያሉ፤ ራዕ.21፡1። በኃጢአት የተበከለው አሮጌው ሰማይና ምድር ይጠፋል። ብሉይ ኪዳን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚመጣ ተንብዮአል፤ ኢሳ.65፡17፤ 66፡22፤ መዝ.101፡25-26።

ለ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ትወጣለች፤ ራዕ.21፡2። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የክርስቶስ ሙሽራ ናት፤ ራዕ.19፡7-8። የእግዚአብሔር መኖሪያ በሰዎች መካከል ይሆናል፤ ራዕ.21፡3። ይህ በ2 ቆሮ.5፡17 ከተገለፀው አዲስ ሕይወት ጋር ተመሳሳይ ነው።

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ክብር የለበሰች ክብርት ከተማ ትሆናለች። እግዚአብሔርና ክርስቶስ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ይሆናሉ። እግዚአብሔርና በጉ ክርስቶስ መብራት ስለሚሆኑ በኢየሩሳሌም ብርሃን አያስፈልግም፥ ስቃይ፥ እንባና ሐዘን በዚያ አይኖርም።

ሐ. አዲስ ገነት ይሆናል፤ ራዕ.22፡1-5። ኤደን ገነትን ይመስላል፤ ዘፍ. 21፡10፤ ሕዝ.47፡8-11። እንደ ብርሌ የሚያንፀባርቀው የሕይወት ውኃ ወንዝ ከእግዚአብሔር ዙፋን ይፈሳል። የሕይወት ዛፍ በየወሩ የተለያየ ፍሬ ይሰጣል። የዛፉም ቅጠሎች አሕዛብን ኃጢአት ካመጣው ብጥብጥና መከፋፈል መፈወሻ ነው። እኛ በዚያ የምንኖር የክርስቶስን ፊት እናያለን፤ ስሙም በግንባሮቻችን ላይ ይሆናል። ጌታ አምላክ እራሱ ስለሚያበራልን ሌሊት አይሆንም። ኃጢአት፤ ርኩሰት ወይም የተጠቀሰው እርግማን ምናልባትም በመጀመሪያው ገነት የመጣውን እርግማን ያመለክት ይሆናል፤ ዘፍ.3፡14-19። ከዘላለም እስከ ዘላለም እንነግሣለን፤ ራዕ.11፡15።

3. ለሰው የተሰጠ የመጨረሻው መልእክት፡-

ሀ. ይህ የሚመጣው መገለጥ እውነት ነው፤ ራዕ.22፡6-7፥ 16-19።

ለ. ክርስቶስ በቶሎ ይመጣል፤ ራዕ.22፡6-7፥ 10-12፥ 20።

ሐ. ቅድስና አስፈላጊ ስለሆነ ተዘጋጁ፤ ራዕ.22፡10-15።

መ. ከዚህ ት.ቢት ምንም እንዳይቀነስ ወይም እንዳይጨመር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል፤ ራዕ.22፡18-19።

ሠ. መጽሐፉ በቡራኬ ይደመድማል፤ ራዕ.22፡21።

## ጥያቄዎች

1. የአሁኑ ሰማይና ምድር ምን ይሆናሉ? ለምን?
2. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ያሉት እነማን ናቸው?
3. የአዲሲቱ ኢየሩሳሌምና የአዲሲቱ ገነት ልዩ ባሕርይ ምንድን ነው?
4. እግዚአብሔር በዮሐንስ ራዕይ ለሰው ልጅ የሰጣቸውን አምስት የመጨረሻ መልእክቶች ከልሱ።

## ማጠቃለያ

ስለ አዲሱ ፍጥረት፥ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና አዲሲቱ ገነት የተገለጸው ሁሉ ባይገባንም እንኳ አሁን ከምናስበው በላይ አስደናቂ እንደሚሆን እናምናለን፤ ሮሜ 11፡33፤ 1ኛ ቆሮ.2፡9። ትንቢትን ማጥናት ያንፃል፤ ስለ ክርስቶስም መመለስ ጉጉት እንዲኖረን ያደርጋል።

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና!»

## ተጨማሪ መግለጫዎች

ንጹሕ ያልሆነ ሰው በመንግሥተ ሰማይ አይኖርም፤ ኤፌ.5፡5፤ ገላ.5፡2።

ለአሸናፊዎች ሽልማት ይሰጣል፤ ራዕ.2፡11፥ 17፥ 26፥ 27፤ 3፡4-5፥ 12፥ 21።

## የጥናት አንድ ጥያቄዎች መልሶች

1. ጥናት አንድ ቁጥር 2 ተመልከቱ።
2. ማቴ. 16፡16።
3. የሐዋ.2፡42።
4. የሐዋ. 7፡38።
5. ጥናት አንድ ቁጥር 3 መ ተመልከቱ።

## የጥናት ሁለት ጥያቄዎች መልሶች

1. ማቴ.16፡16-18፤ 28፡18-20፤ የሐዋ.1፡8፤ 13፡2-3።
2. ጥናት ሁለት ቁጥር 1 ተመልከቱ።
3. የሐዋ.13፡1-4።
4. ጥናት ሁለት ቁጥር 2 ተመልከቱ።

## የጥናት ሦስት ጥያቄዎች መልሶች

1. 1ኛ ቆሮ.12፡13።
2. 1ኛ ቆሮ.12፡27-28።
3. 1ኛ ቆሮ.12፡22-26።
4. ኤፌ.5፡25-27።
5. ጥናት ሦስት ቁጥር 3 ተመልከቱ።

## የጥናት አራት ጥያቄዎች መልሶች

1. ኤፌ.2፡11።
2. ኤፌ.2፡12።
3. ኤፌ.2፡18-22።

## የጥናት አምስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ጥናት አምስት ቁጥር 1 ተመልከቱ።
2. ጥናት አምስት ቁጥር 3 ተመልከቱ።
3. 2ኛ ተሰ.3፡14-15።
4. ኤፌ.5፡26-27።
5. 2ኛ ቆሮ.2፡14።

## የጥናት ስድስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ኤፌ.4፡7፤ ሮሜ 12፡3-5።
2. ሮሜ 12፡11።
3. ኤፌ.4፡12-14።
4. ኤፌ.4፡13-16።

5. ኤፌ.4፡15-16።

## የጥናት ሰባት ጥያቄዎች መልሶች

1. ሮሜ 6፡3-4።
2. የሐዋ.16፡16፥ 30-31፤ ሉቃስ 23፡23።
3. ማቴ.3፡15፤ ዮሐ.1፡33፤ መዝ.39፡7-8፤ ዕብ.10፡7።

## የጥናት ስምንት ጥያቄዎች መልሶች

1. ኢየሱስ። በመጨረሻው ምሽት።
2. ጥናት ስምንት ቁጥር 2 ሀ፤ ለ፤ ሐ፤ ተመልከቱ።
3. ጥናት ስምንት ቁጥር 4 ተመልከቱ።

## የጥናት ዘጠኝ ጥያቄዎች መልሶች

1. ጥናት ዘጠኝ «ሐዋርያት» የሚለውን ክፍል ተመልከቱ።
2. የቤ.ክ. ኅብረት፥ ዕድገትና ጉልምስና ይደናቀፋል።
3. ዲያቆናትና ሽማግሌዎች በሚሉት ርዕሶች ሥር የተሰጡትን ዝርዝሮች እንደገና ተመልከቱ።
4. 1. ማስተማርና ወንጌልን ማሠራጨት፥
   2. ትምህርተ - ክርስትና የተሳሳተ ትርጉም እንዳይሰጠውና በተግባርም መተርጎሙን መከታተል፥
   3. ሥነ - ምግባርን መቆጣጠር።
5. በቤተ ክርስቲያኒቱ የውስጥ ደንብ መሠረት ሊመረጡ ይችላሉ።
6. ጉባኤው።
7. ሽማግሌዎች በመመሪያቸው መሠረት መሥራታቸውን ማረጋገጥና ትምህርታቸው አእግዚአብሔር ቃል መመዘን።

## የጥናት አሥር ጥያቄዎች መልሶች

1. ዘፍ.1፡28፤ 2፡18።
2. ቆላ.3፡17-19።
3. ግላዊ ገለጻን ይጠይቃል።

## የጥናት አሥራ አንድ ጥያቄዎች መልሶች

1. መልሱን ከኤፌ.5፡23 ፈልጉ፤ የተሰጠውን መመሪያ በመርሳታቸው ነው።
2. ኤፌ.5፡25ን ተመልከቱ።
3. ኤፌ.5፡22፥ 24ና 33፤ ዘፍ.2፡18ን ተመልከቱ፤ ለጌታ ቃል ሳይታዘዙ ሲቀሩ ነው።
4. ኤፌ.5፡22ና 33 ተመልከቱ።
5. ከክርስቶስ የበላይነት ሥልጣን ጋር ነው፤ ኤፌ.5፡24።

6. መልሱን ከኤፌ.6፡4 ፈልጉ። በሰላም እንዲኖሩ ነው፤ ኑሮአቸው የተስተካከለ አይሆንም።

## የጥናት አሥራ ሁለት ጥያቄዎች መልሶች

1. 2ኛ ቆሮ. 6፡14ን ተመልከቱ።
2. በማቴ.19፡9 ላይ ተገልጿል።
3. መልሱን በማቴ.19፡12 ውስጥ ፈልጉ።
4. ማቴ.19፡8ን ተመልከቱ።

## የጥናት አሥራ ሦስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ደካሞች መሆናችንን ስንረዳ ብቻ ጌታ ሊያግዘን ይችላል፤ ዮሐ.15፡5።
2. መዝ.138፡7-10።
3. ያለ እምነት ምንም ነገር መቀበል ስለማንችል ነው።
4. በይበልጥ በጌታ መታመንን እንለማመዳለን።

## የጥናት አሥራ አራት ጥያቄዎች መልሶች

1. መልሱን ከፊል.4፡6-7ና 1ኛ ጢሞ.2፡1-2 ፈልጉ።
2. ሰላም እንዲሰፍን ነው፤ 1ኛ ጢሞ.2፡1-3።
3. ብዙ ለውጦች ይታያሉ፤ ለምሳሌ ፊል.4፡6-7፤ 1ኛ ዮሐ.1፡9፤ ኤፌ.1፡17-19 ተመልከቱ።
4. በጸሎት ሳቢያ ኃይሉን መግለጥ ስለሚችልና የሚሰማና የሚሠራ መሆኑን በይበልጥ ስለሚገልፅ ነው።
5. እርሱ የሚንከባከበን መሆኑን ተረድተን እንድናከብረው ነው፤ በፈቃደኝነት የበላይ ሥልጣኑን እንድናሳውቅ ይፈልጋል።

## የጥናት አሥራ አምስት ጥያቄዎች መልሶች

1. አለማመን፥ አለመጠየቅ፥ መጠራጠር፥ ስግብግብነት፥ አለመታዘዝ፥ ወዘተ።
2. በሥጋቸው ድካም ስለተሸነፉ ነው፤ የሥጋችንን ድክመቶች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ባለማሸነፋችን ሊሆን ይችላል።
3. ከሁሉ አስቀድመን ኃጢአታችንን መናዘዝ ይኖርብናል።
4. ተማሪዎች የሚያቀርቡአቸው ሐሳቦች መልሶች ይሁኑ።

## የጥናት አሥራ ስድስት ጥያቄዎች መልሶች

1. በዮሐ. 17፡21፥ 23ና 26 ውስጥ ይገኛሉ።
2. አንድነታችንን ለዓለም እንድንገልጽ የክርስቶስ ፈቃድ ነው።
3. ሀ. ዮሐ.17፡1።

ለ. ዮሐ.17፡17-19።

## የጥናት አሥራ ሰባት ጥያቄዎች መልሶች

1. ከእግዚአብሔር አባታችን የግል ግንኙነትን የማድረግ ፍላጎት መሆን አለበት፤ ማቴ.6፡6።
2. መልሶችን ከማቴ.6፡9-10 ፈልጉ።
3. መልሶቹን ከማቴ.6፡11፥ 12ና 13 ፈልጉ።

## የጥናት አሥራ ስምንት ጥያቄዎች መልሶች

መልሶቹን ከገጽ 27 ገልብጡ።

## የጥናት አሥራ ዘጠኝ ጥያቄዎች መልሶች

1. መልሱን ከ1ኛ ቆሮ.15፡55-57 ፈልጉ።
2. የሞቱት ሰዎች የሚያርፉበት ሥፍራ ነበር፤ ሉቃስ 16፡22-26።
3. እንቅልፍ ተብሏል፤ 2ኛ ቆሮ.5፡6-8፤ ፊል.1፡23።
4. 1ኛ ተሰ.4፡16 ተመልከቱ።
5. የመጨረሻ ፍርድ ነው፤ ራዕ.2፡11፤ 20፡6።
6. ከሞት ወደ ሕይወት ስለተሻገሩ ነው፤ ዮሐ.5፡24።

## የጥናት ሃያ ጥያቄዎች መልሶች

1. መልሱ ከ1ኛ ቆሮ.15፡12፥ 19ና 29 ፈልጉ።
2. ክርስቶስ በሥጋ ከተቀበረበት መቃብር መነሣቱ ነው፤ 1ኛ ቆሮ.15፡3-6።
3. ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችን መሠረተቢስ ነው፤ 1ኛ ቆሮ.15፡13-19።
4. ብዙ ሰዎች አይተውታል፤ 1ኛ ቆሮ.15፡6።
5. በሥነ ምግባራዊ ሕይወታቸው ለዚያ ዕለት ዝግጁ ሆነው የመገኘት ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ አለበት።

## የጥናት ሃያ አንድ ጥያቄዎች መልሶች

1. 1ኛ ተሰ.4፡14-18 ተመልከቱ።
2. ተማሪዎቹ ያቀረቡአቸው ሃሳቦች መልሶች ይሁኑ።
3. መልሳችሁ ከ1ኛ ተሰ.4፡16-17 ውስጥ ከሚገኘው ጋር የቱን ያህል እንደሚዛመድ ተመልከቱ። ማቴ. 24፡26ን ተመልከቱ።
4. ይህ ጥያቄ ብዙ መልሶች ይኖሩታል፤ እናንተ ስንቶቹን አግኝታችኋል?

## የጥናት ሃያ ሁለት ጥያቄዎች መልሶች

1. ሀ. ማር.14፡62፤ ለ. ማቴ. 24፡36፤ ሐ. ማር. 13፡35።
2. እነዚህ ኪዳኖች ምን ያህል እንደተፈጸሙ የሚያቀርቡአቸው ሐሳቦች የተለያዩ ናቸው።
3. በመታዘዝ ላይ የተመሠረተ ነው።

4. የዚህን ጥናት ነጥብ 2 ክፍል ሐ ተመልከቱ፤ በዚያ ከሚገኘው መረጃ ጋር መልሳችሁን አነፃፅሩ።

5. አገሩን የመውረስ ተስፋ ነው።

## የጥናት ሃያ ሦስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ዮሐ.14፡3ና 1ኛ ዮሐ.3፡1-3 ተመልከቱ።

2. ነጥብ 2 ክፍል ሀ፥ ለ፥ ሐ እና መ ተመልከቱ።

3. በማንኛውም ወቅት ሊመለስ ይችላል ብሎ የሚያምነው ክፍል ነው።

## የጥናት ሃያ አራት ጥያቄዎች መልሶች

1. ማቴ.7፡21ና 2ኛ ቆሮ.6፡2 ተመልከቱ።

2. ሥራቸውን በመገምገም ነው፤ ማቴ.25፡15ና 21።

3. መልሱን ከማቴ.25፡28-29 ፈልጉ።

4. የእግዚአብሔርን ኃይል መግለጽ ነው፤ ማቴ.5፡5፤ ያዕ.2፡17፤ 1ኛ ጴጥ.2፡12ና ማቴ.26፡7-10።

5. ዲያብሎስና እኛን የሚኮንነው ሕግ፤ ዕብ.2፡14፤ ቆላ.2፡13-15።

6. ራዕ.20፡10-15 ተመልከቱ።

7. ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ንስሐ በመግባት ይቅርታ መቀበል እንዲችሉ ነው።

## የጥናት ሃያ አምስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ይጠቀለላሉ፤ ራዕ.22፡3።

2. የእግዚአብሔር ቤተሰብ ብቻ ናቸው፤ ራዕ.19፡7-8፤ 21፡2።

3. ራዕ.21፡4ና 22፡3ና 5 ተመልከቱ።

4. ቁጥር 3 ሀ-ሠ ተመልከቱ።